# እውነተኛውና
# የመጨረሻው መልዕክት



1201008

## ማውጫ


መቅድም 1

1. ኢስላም ምንድነው? 2

2. በአንድ አምላክ ማመን 3

ሀ. ምንም የማይሳነው አላህ በጌትነቱ ብቸኛ ከመሆኑ አንጻር 4

ለ. የአምልኮ ተግባራት ሁሉ ለአንድ አላህ ብቻ የሚገባው ከመሆኑ አንፃር 6

ሐ. በስሞቹና በባህሪያቱ ከፍጡራን ሁሉ የተለየ ከመሆኑ አንፃር 9

3. ስድስቱ የእስልምና እምነት መሠረቶች 11

ሀ. በአላህ ማመን 11

ለ. በመላዕክቱ ማመን 12

ሐ. ባወረዳቸው መጽሐፍት ማመን 12

መ. በነቢያቱና በመልዕክተኞቹ ማመን 14

ሠ. በመጨረሻው (በፍርዱ) ቀን ማመን 17

ረ. በመለኮታዊ ፍርዱና ውሳኔው (ቀደር) ማመን 19

4. የሰው ልጅ የፈለገውን መርጦ የማድረግ መብቱ 20

5. በኃይማኖት ማስገደድ የለም 22

6. አምስቱ የኢስላም ማዕዘናት 22

ሀ. ሸሀዳ 23

ለ. ሰላት 25

ሐ. ዘካዕ 26

መ. ፆም 26

ሠ. ሐጅ 27

7. ቁርዓን 28
8. ነቢዩ ሙሀመድና ሱናቸው 32
9. በኢስላም ስም ፈጠራን (ቢድዓን) የማስፋፋት አደጋ 34
10. የአደምና የሐዋ ታሪክ 36
11. እየሱስ 39
12. ኃጢያትና ንሰሐ (ተውባህ) 41
13. የኢስላም ድርጅታዊ መዋቅር 43
14. ኢስላማዊ ሕግ 45
15. ኢስላማዊ የአለባበስ ሥርዓት 48
16. ሴቶች በኢስላም 50
17. የወንድ ትምክህተኝነትና የሙስሊሙ ዓለም 52
18. ኢስላም፣ ጦርነትና ጂሃድ 55
19. ሳይንስና ቴክኖሎጂ 63
20. አክራሪነትና አሸባሪነት 65
21. ማጠቃለያ 70
22. የፀሐፊው ማስታወሻ 72

ስለ ኢስላም ተጨማሪ መረጃ ካስፈለገ፡-

www.islam _is.com

www.islam _guide.com

www.it_is_truth.org

www.qf.org

www.islam101.com

www.discoverislam.com

www.99_names.com

www.islamtomorrow.com

www.iad.org

# መቅድም

የዚህ ጽሑፍ ዓላማ የኢስላምን ትክክለኛ አስተምህሮቶችን ማቅረብ ነው:: ስለ ኢስላም ማንኛውንም ዓይነት ቁንፅል ገጽታ ወይም የተለየ ትርጓሜ አናቀርብም:: የምናቀርበው ያለምንም መሸፋፈንና መሸራረፍ ኢስላምን እንዳለ ነው:: አተገባበሩም ነቢዩ ሙሀመድ ባሳዩን መንገድ ብቻ ነው:: ፍላጎታችንም ይህንን የኢስላም መንገድ በቁርዓን እንደ ተቀመጠውና በነቢዩ ሙሀመድ (ሰ.ዐ.ወ.)[1] እንደተተገበረው ማቅረብ ነው:: በተጨማሪም ስለ ኢስላም በተደጋጋሚ የሚነሱ ጥያቄዎችን ለመመለስ እንሞክራለን::

ከጠቅላላው የዓለም ህዝብ አንድ አምስተኛ የሚሆነው ሙስሊም ቢሆንም ምዕራቡ ዓለም ኢስላምን በቅጡ ሳይረዳ የተሳሳተ ምስል ሲሰጠው ይስተዋላል:: ይህ ሥራም ኢስላምን ለነቢዩ በወረደው መልኩ በማቅረብ በተለምዶ በተያዘው ኢስላምን በጭፍን የመጥላት አባዜ የሚገፍ ብርሃን ይፈነጥቃል ብለን እናስባለን:: ይህንን ጽሑፍ የጻፍነው የሌሎች እምነት ተከታዮችም ይህች ዓለም መቻቻል፣ ደግነት፣ ስምምነትና ሰላም የሰፈነባት እንድትሆን ለምናደርገው ጥረት ከጎናችን ይሰለፋሉ በሚል እምነት ነው::

---

[1] ሰ.ዐ.ወ ማለት ሰላትና ሠላም በነቢዩ ላይ ይውረድ ማለት ነው:: በሁሉም ነቢያትና መልዕክተኞች ላይ ሰላም ማውረድ በኢስላም የተወደደ ተግባር ነው፣ የአላህ መልዕክተኞችን ማክበር አላህን ማክበር ነውና::

## 1. ኢስላም ምንድን ነው?

ኢስላም የሚለው የዐረብኛ ቃል ጥሬ ትርጉሙ እጅ መስጠት ወይም መማረክ ማለት ሲሆን በኃይማኖታዊ ትርጓሜው ደግሞ አንድ ሰው በሰላምና በተረጋጋ መንፈስ ይኖር ዘንድ ከልብና በሙሉ ፈቃደኝነት ለአላህ እጅ መስጠት ማለት ነው። አላህ ፍትህ፣ እውነትና ሰላም በመሆኑ ሰላም (በሂብሩ ሻሎም፣ በእንግሊዝኛ ፒስ) የሚገኘው ከአላህ የወረዱ ትእዛዝን በፍፁም ታዛዥነት በመፈፀም ነው።

ኢስላም[2] የሚለው ስያሜ ዓለም አቀፋዊ ትርጓሜ የያዘ ነው። የአይሁድ እምነት ከይሁዳ፣ የክርስትና እምነት ከክርስቶስና የቡድሃ እምነት ከቡድሃ ስያሜያቸውን ያገኙ ሲሆን የኢስላም ስያሜ ግን ከግለሰብም ሆነ ከጎሳ ስያሜ በግለሰቦች የተመረጠ አይደለም። ኢስላም የሚለው መጠሪያ ከዓለማት ጌታ ለሰው ልጆች የህይወት ጎዳና ዓለም አቀፍ እምነት የተሰጠ ስያሜ ነው። ኢስላም የመላው ዓለም እንጂ የምዕራብም የምሥራቅም ኃይማኖት አይደለም። ኢስላም ሙሉ ለሙሉ እጅ መስጠትን የሚያመለክት የተሟላ የህይወት መንገድ ነው። ፍላጎቱን በፈቃደኝት[3] ሙሉ በሙሉ ለአላህ ያስገዛ ሰውም ሙስሊም ይባላል። በዚህ የኢስላም መንገድ ለመጀመሪያ ጊዜ የተጓዙት ነቢዩ ሙሀመድ ሳይሆኑ አባታችን አደም ናቸው። ከአደም በኋላም

---

[2] ኢስላም ትኩረቱ መንፈስ ላይ ብቻ ስላልሆነ፤ አንዳንድ ሙስሊሞች ኢስላምን "ኃይማኖት" ብሎ መጥራት ተገቢ አይደለም ይላሉ። ኢስላም በዐረብኛ ዲን (የሕይወት መንገድ) ተብሎ ይገለጻል። ይህም እምነታቸውን «መንገድ» ብለው ይጠሩ ከነበሩት የጥንት ክረስቲያኖች ጋር አንድ ነው።

[3] በፈቃደኝነት የሚለው አገላለፅ በዚህ አገባቡ ያስተቃውሞ ከሚለው ከፍ ያለ ትርጓሜ የያዘ ነው። ይህም ማለት ያለምንም ድብቅ ዓላማ ወይም ቁጥብነት ከልብ በመነጨ ፍላጎት ለአላህ እጅ መስጠት ማለት ነው።

በርካታ ነቢያትና መልዕክተኞች የአላህን ትዕዛዛት ለሰው ልጆች ግልፅ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል፡፡ አላህ የመጨረሻውን ነቢይ (ሙሀመድን) መርጦ የመጨረሻውን መመሪያ (ቁርዓንን) እስኪልክ ድረስ ከተላኩበት ወቅት ጋር የሚስማማ ትምህርት ሰጥተዋል፡፡

*አላህ* የሚለው የዐረብኛ ቃል ሰማያትንና ምድርን ለፈጠረው አምላክ የተሰጠ ስያሜ ነው፡፡ ትርጉሙም *"እውነተኛና ብቸኛ የሆነ ጌታ"* ማለት ነው፡፡ ዐረብኛ ተናጋሪ የሆኑ አይሁዶችና ክርስቲያኖችም አምላክን የሚጠሩት *አላህ* ብለው ነው፡፡ በኢስላም «አላህ» የሚለው ቃል ፍጥረታት ሁሉ ሊያመልኩትና ሊገዙት ለሚገባው ብቸኛ አምላክ ስሞችን በሙሉ አጠቃሎ የያዘ ትልቁና ዋናው መጠሪያ ነው፡፡

## 2. በአንድ አምላክ ማመን

በአንድ አምላክ ማመን (በዐረብኛ *ተውሂድ* በመባል የሚታወቀው) በእስልምና ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡ በአስርቱ ትዕዛዛትም በአንድ አምላክ ማመን፣ ትኩረት ተሰጥቶት በመጀመሪያ ደረጃ የተቀመጠ ነው፡፡ የኢስላም ትምህርቶችና እሳቤዎች የአምላክ አንድነትን መሠረት አድርገው የተገነቡ ናቸው፡፡ የኢስላም ጥሪ ዓላማም ሰዎች ፍጡራንን ከመገዛት ወጥተው ብቸኛና እውነተኛ የሆነውን አንድ አላህን ወደ መገዛት እንዲመለሱ ማድረግ ነው፡፡ ማንኛውም የአምልኮና የመገዛት ተግባር *አንድ አምላክን ብቻ* ከመገዛት ያፈነገጠ ከሆነ ትርጉምም ሆነ ዋጋ አይኖረውም፡፡

ከአስፈላጊነቱ የተነሳ በአንድ አምላክ ብቻ የማመን እሳቤ (በመለኮታዊነቱና በብቸኛነቱ) በአግባቡና ሙሉ በሙሉ መረዳት ያሻል:: ለማብራራት ያመች ዘንድ በአንድ አምላክ ብቻ ማመን የሚለውን በሦስት እይታዎች አንፃር ልንመለከተው እንችላለን::

ሀ. ምንም የማይሳነው አላህ በጌትነቱ ብቸኛ ከመሆኑ አንፃር

ለ. የአምላክ ተግባራት ሁሉ ለአንድ አላህ ብቻ የሚገባው ከመሆኑ አንፃርና

ሐ. በስሞቹና በባሕሪያቱ ከፍጡራን ሁሉ የተለየ ከመሆኑ አንፃር

ይህ አከፋፈል አላህ ብቸኛና ከፍጥረታት ሁሉ የተለየ ጌታ ነው ለሚለው ሃሳብ ብቸኛ የማስረጃ መንገድ ሊሆን አይችልም:: ነገር ግን ይህ አከፋፈል ርዕሰ-ጉዳዩን ተንትኖ በማየት በቀላሉ ለመረዳት ሊያግዝ ይችላል:: አንድ አምላክ ብቻ የማምለክ እሳቤ ኢስላምን በአግባቡ ለመረዳት ቁልፍ በመሆኑ ትኩረት ሰጥቶ በጥልቀት መረዳት ያሻል::

ሀ. ምንም የማይሳነው አላህ በጌትነቱ ብቸኛ ከመሆኑ አንፃር

አላህ ብቸኛ የፍጥረታት ባለቤት ነው ስንል ለማያትንና ምድርን ከሌሉበት ያስገኘው አላህ በዓለም ላይ ፍፁምና ምሉዕ የሆነ የበላይነት አለው ማለታችን ነው:: ፍጥረታትን ሁሉ ያስገኘው እሱ ብቻ ነው:: ሁሉ ነገር እውን እንዲሆን የሚያደርገው፣ ህይወት የሚሰጠውና የሚነሳው አላህ ብቻ ነው:: አላህ ኃያል፣ ፍፁም፣ ከማንኛውም ጉድለትና ስህተት የፀዳና

ሁሉን ማድረግ የሚችል ብቸኛ ጌታ ነው:: ልዕልናውን የሚጋራ ማንም የለም:: የወሰነውንም የሚሽር ኃይል የለም::

አላህ እያንዳንዳችንን ከነጠላ ህዋስ አንስቶ አሁን ያለንበት ሁኔታ ላይ እንድንገኝ ያደረገን ብቸኛ አምላክ ነው:: ከ100 ቢሊዮን በላይ ጋላክሲዎች አንስቶ እስከ ኤሌክትሮኖችና ኒውትሮኖች በውስጣቸው ያሉትን ቅንጣቶችንም ጭምር የፈጠረ እንዲሁም የተፈጥሮ ህግ ተመናቸውንና ሚዛናቸውን ጠብቀው እንዲቆዩ ያደረገ ነው:: *አንድም የዛፍ ቅጠል አይወድቅም እሱ የሚያውቀው ቢሆን እንጂ::* አላህ ዘንድ እያንዳንዱ ነገር በግልፅና በተሟላ መልኩ ተመዝግቧል::

እሱ ልናስበው ከምንችለው በላይ እጅግ የላቀ ነው:: እጅግ ኃያል የሆነ፣ አንድን ነገር መፍጠር በሻ ጊዜ *"ሁን"* በሚል ቃል ብቻ ሊያስገኝ የሚችል ጌታ ነው:: ጊዜን፣ ቦታን፣ የሚታወቁና የማይታወቁ ነገሮችን ሁሉ የፈጠረ ነገር ግን እርሱ ከፍጥረታት አካል ያልሆነ ነው:: አብዛኞቹ እምነቶች ዓለማትን ያለአጋር ያስገኘው አንድ አምላክ መሆኑን ይቀበላሉ:: በዚህ ሃሳብ ላይ ኢስላም አላህ ፈጣሪ እንጂ ከፍጡራን መሀል አንዱ አለመሆኑንና ከሥልጣኑም የሚጋራ ምንም ፍጡር እንደሌለ ይጨምራል:: ከፍጡራኑ ውስጥ የአላህን ኃይልና *ሥ*ልጣን የሚጋራ አለ ብሎ ማመን ከክህደትና ከባዕድ አምልኮ ይቆጠራል:: *"እድል ጠቋሚዎችና"* ከከብ ቆጣሪዎች ወደፊት የሚሆነውን ያውቃሉ ብሎ ማመንም ከተሳሳተ እምነትና ከክህደት ይመደባል:: ምክንያቱም ሁሉን አዋቂ የሆነው አላህ እንዲህ ይላል:- *«ወደፊት የሚሆነውን የሚያውቅ እሱ /አላህ/ ብቻ ነው::»*

መለኮታዊ እርዳታ መስጠት የሚችለውም አንድ አላህ ብቻ ነው:: አስማትም ሆነ አሽንክታብ መልካም እድል ያመጣሉ ብሎ መማን ባዕድ አምልኮ ነው:: እንደነዚህ ዓይነት የተሳሳቱ እምነቶች በኢስላም ቦታ የላቸውም::

### ለ. የአምልኮ ተግባራት ሁሉ ለአንድ አላህ ብቻ የሚገባው ከመሆኑ አንፃር

ከአደም ጀምሮ ለሰው ልጅ የተላኩት ነቢያትና መልዕክተኞች ለዘመናት ሲሰብኩት የኖሩት አምልኮ የሚገባው ፍፁም ለሆነው አንድ አላህ ብቻ መሆኑን ነው:: አላህ ፍጥረታትን የፈጠረበት ዓላማ እሱን ብቻ እንዲገዙት መሆኑን ገልጿል:: የኢስላምም ዓላማ የሰው ልጆች ፍጡርን ከመገዛት አንድ ፈጣሪ ብቻ ወደ መገዛት መጥራት ነው:: ኢስላም ከሌሎች እምነቶች የሚለይበት ዋናው ነጥብም ይህ ነው:: ምንም እንኳን አብዛኞቹ እምነቶች ዓለምን የፈጠረ አንድ ፈጣሪ መኖሩን ቢመሰክሩም ከባዕድ አምልኮ ሙሉ በሙሉ የፀዱ ሆነው አይገኙም:: እነዚህ እምነቶች ለተከታዮቻቸው ከአላህ በታች ኃይል አላቸው ብለው የሚያምኗቸውን ፍጥረታት እንዲገዙ አለዚያም አማላጅ አድርገው እንዲይዟቸው ይሰብካሉ::

ሆኖም ከአደም ጀምሮ እስከ ሙሀመድ /ሰ.ዐ.ወ/ የተላኩት ነቢያት ሁሉ ያስተማሩት የሰው ልጅ አላህን ብቻ ያለ አጋርና ያለ አማላጅ እንዲያመልክ ነው:: ይህ የጠራ፣ ለማመን የማይከብድ፣ ቀላልና ከሰው ልጅ ተፈጥሮአዊ ባሕሪይ ጋር የሚጣጣም እምነት ነው:: ሥነ-ባህል የሚያጠኑ ባለሙያዎች የሰው ልጅ የእምነት ጉዞ ከባዕድ አምልኮ አንድ አምላክን ወደ ማምለክ ሄዷል ብለው ያስባሉ:: ይህንን እሳቤ ኢስላም በፅኑ ይቃወማል:: ኢስላም

በተቃራኒው የሰው ልጅ የእምነት ጉዞ አንድ አምላክን ብቻ ከመገዛት ወደ ባዕድ አምልኮ መለወጡን ያስገነዝባል። ምንም እንኳን ነቢያት በመሃከላቸው እያሉም በጌታ የሚያጋሩና የነቢያት ማስጠንቀቂያን ጥሰው ሰዎችን ወደ ባዕድ አምልኮ የሚጣሩ የነበሩ ቢሆንም የሰው ልጅ እምነት ባዕድ አምልኮ ውስጥ ሙሉ በሙሉ የሚዘፈቀው በሁለት ነቢያት መካከል በሚኖር የጊዜ ክፍተት ነበር። በዚህም ምክንያት የሰው ልጆች ከባዕድ አምልኮ ተላቀው ከተፈጥሮአዊ ባህሪያቸው ጋር ወደሚስማማው አንድ አምላክን እንዲገዙ ወደሚያዘው እምነት እንዲመለሱ የሚያስተምሩ ነቢያት በተከታታይ ተልከላቸዋል።

አላህ የሰው ልጅን የፈጠረው በውስጡ እሱን ብቻ የማምለክ ተፈጥሮአዊ ዝንባሌ እንዲኖረው አድርጎ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ሸይጣን በተቻለው መንገድ ሁሉ ሰዎች አንድ አላህን ብቻ ከመገዛት ፍጡራንን ወደ መገዛት እንዲያዘነብሉ ይጎተጉታል። ምንም እንኳን ፈጣሪ በአእምሮአቸው ሊስሉትና ሊያስቡት ከሚችሉት በላይ መሆኑን በልቦናቸው ቢያውቁም ብዙ ሰዎች በህሊናቸው የሳሉትን የመዳሰስና የሚታይ ነገር ወደ ማምለክ ይዘነብላሉ።

በሰው ልጅ የታሪክ ሂደት ውስጥ ሰዎች አንድና ትክክለኛ አምላክን ብቻ እንዲገዛ ጥሪ የሚያደርጉ ተከታታይ ነቢያትና መልዕክተኞች ተልከዋል። ነገር ግን በሸይጣን ጉትጎታ ምክንያት ሰዎች በተደጋጋሚ ፍጡራንን በማምለክ በባዕድ አምልኮ ተግባር ተዘፍቀዋል።

አላህ የሰው ልጅን የፈጠረው እሱን ብቻ እንዲገዛው ነው:: በኢስላም ትልቁ ወንጀል ወደ አላህ ይበልጥ ለመቃረብ ታስቦ እንኳን ቢሆን ከአላህ ውጭ ያለን ማንኛውም ነገር ወይም ማንኛውም ሰው መገዛት ወይም ማምለክ ነው:: በራሱ የተብቃቃው አላህ ምንም ዓይነት አማላጅ አያስፈልገውም:: አላህ ፀሎታችንን በሙሉ የሚሰማና ስለሚሆኑ ነገሮች ሁሉ የተሟላ ዕውቀት ያለው ጌታ ነው::

ይህ ከመሆኑም ጋር የኛ አምልኮ ለአላህ ምንም የሚጠቅመው ነገር የለም:: ሆኖም ሰዎች እሱን ብቻ መገዛታቸው እንደሚያስደስተው ገልጿል:: እሱ በምንም ነገር ላይ ጥገኛ ያልሆነ ጌታ ነው:: ነገር ግን ፍጥረታት በሙሉ በሱ ላይ ጥገኞች ናቸው::

በዓለም ላይ የሚገኙ ሰዎች ሁሉ በአንድ ላይ ተሰብስበው እሱን ብቻ ቢገዙት ቅንጣት ታህል የሚጠቅመው ነገር የለም፤ በልዕለ-ኃያልነቱ ላይም የብናኝ ክብደት ታህል እንኳን አይጨምርም:: በሌላ በኩል ፍጡራን በሙሉ እሱን ከመገዛት ቢያምፁ ከልዕለ-ኃያልነቱ ላይ የሚቀንሰው ቅንጣት ያህል ነገር የለም:: አላህን ስንገዛ የተፈጠርንበት ቅዱስ ዓላማን በማሳካት /የተፈጥሮ ጥያቄአችንን በመመለስ/ እኛው ራሳችን እንጠቀማለን:: አላህ ፍፁምና ዘላለማዊ ስለሆነ ከኛ ምንም አይፈልግም::

አምልኮ እንዲሁ በተለምዶ የሚተገበር ክንውን አይደለም:: አምልኮ ሁሉንም የሕይወት ዘርፍ የሚያካትት ነው:: የህፃን ጨርቅ መቀየር፣ ወላጆችን ማክበርና መንከባከብ፣ እንዲሁም እንቅፋቶችን ከመንገድ ላይ ማስወገድ የመሳሰሉትን ሁሉ ከአላህ ውዴታ ለማግኘት ተብሎ ብቻ የተሠሩ ከሆነ እንደ አምልኮ

ይቆጠራሉ:: ሆኖም ማንኛውም ጥቅም /ሃብትም ሆነ ሥራ፣ ሥልጣንም ሆነ ዕውቀት/ የአላህ ውዴታን ከማግኘት ይበልጥ የሚያሳስበን ከሆነ ተግባራችን ከባዕድ አምልኮ የሚቆጠር ይሆናል::

ሐ. በስሞቹና በባሕሪያቱ ከፍጡራን ሁሉ የተለየ ከመሆኑ አንጻር

በስሞቹና በባሕሪያቱ ከፍጡራን ሁሉ የተለየ ነው ስንል አላህ የፍጡራን ባሕሪያት የሌሉትና ፍጡራንም የፈጣሪ ባሕሪያት የሌላቸው መሆኑን ለማመልከት ነው:: አላህ በባሕሪያቱ ሁሉ ከፍጡራን ፍፁም የተለየ ነው:: የሁሉም ነገር ፈጣሪ በመሆኑ ምንም ዓይነት ገደብ ሊደረግለት አይችልም::

*"አላህ ከእርሱ በቀር ሌላ አምላክ የለም፣ ሕያው፣ ራሱን ቻይ ነው፣ ማንገላጀትም፣ እንቅልፍም አይዘውም፣ በሰማያት ውስጥና በምድር ውስጥ ያለው ሁሉ የርሱ ብቻ ነው፣ ያ እርሱ ዘንድ በፍቃዱ ቢሆን እንጂ የሚያማልድ ማነው? /ከፍጡሮች/ በፊታቸው ያለውንና ከኋላቸው ያለውን ሁሉ ያውቃል፣ በሻውም ነገር እንጂ ከዕውቀቱ በምንም ነገር አያካብቡም /አያውቁም/፣ መንበሩ ሰማያትንና ምድርን ሰፋ፣ ጥበቃቸውም አያቅተውም፣ እርሱም የሁሉ በላይ ታላቅ ነው::" /ቁርዓን 2:255/*

በኢስላም የፍጡርን ባሕሪይ ለአላህ መስጠት በጥብቅ የተከለከለ ነው:: ለሱ ልንሰጠው የምንችለው መለያ ባሕሪይ እሱ ራሱን በቁርዓኑ የገለፀውና ነቢዩ /ሰ.ዐ.ወ/ ስለሱ ባሕሪያት በሐዲሳቸው ያብራሩትን ብቻ ነው:: አብዛኛዎቹ የአላህ ስሞችና ባሕሪያት ከሰው ልጅ ስሞችና ባሕሪያት ጋር የሚመሳሰሉ ይመስላሉ:: ይህ ከሰው ልጅ ቋንቋ የመግለፅ ውስንነት የመነጨ

ነው፡፡ ልክ እንደራሱ የአላህ መለያ ባህሪያትም ከምናውቃቸው የፍጡራን ባሕሪያት ሁሉ የተለየ ነው፡፡ ለምሳሌ፡- አላህ መለኮታዊ እወቀት አለው፡፡ ዕውቀቱም ወሰን የሌለው ጥንትም የነበረ፣ የማይቀንስና የማይጨምር እንዲሁም ዘላለማዊ ነው፡፡ የሰው ልጅም ዕውቀት አለው፡፡ የሰው ልጅ ዕውቀት ግን ከጊዜ በኋላ በትምህርትና በልምድ የሚገኝ ውስን የሆነ በየጊዜው የሚቀንስና የሚጨምር እንዲሁም ለስህተትና ለመርሳት የተጋለጠ ጊዜያዊ ነው፡፡

ኃያሉ አላህ መለኮታዊ ፍላጐት አለው፡፡ የሰው ልጅም ፍላጐት አለው፡፡ የአላህ ፍላጎት ሁሌም እውን ከመሆን የሚያግደው ነገር የለም፡፡ እንደ መለኮታዊ ዕውቀቱ ሁሉ ፍላጐቱም በፍጡራኑ ላይ ባለፈው ጊዜ አሁንና ወደፊት እንዲከሰቱ የሻቸውን ነገሮች ሁሉ አጠቃሎ የያዘ ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የሰው ልጅ ፍላጐት ዝም ብሎ ሃሳብና ምኞት ሲሆን እውን ሊሆን የሚችለው አላህ ከፈቀደ ብቻ ነው፡፡

የአላህ ባሕሪይ የሰው ልጅ መለያ በሆኑ ባሕሪያት ሊገለጽ አይችልም፡፡ ምክንያቱም የሰው ልጅ ባሕሪያት ሁሉ ውስን በመሆናቸው ነው፡፡ አላህ ፆታ፣ ድክመት ወይም ጉድለት የለውም፡፡ አላህ ከሰውም ሆነ ከሌሎች ፍጥረታት ፆታዊ ባሕሪይ የጠራ ነው፡፡ በጽሑፉ ውስጥ እሱ እያልን የምንጠራው በአማርኛ ብሎም በሌሎች የሴም ቋንቋዎች ውስጥ ፆታ አልባ ተውላጠ ስም ስለማይገኝ ነው፡፡

በቁርዓን ውስጥ አላህ ራሱን ሲገልጽ «እኛ» የሚለው ተውላጠ ስምን የሚጠቀመው ራሱን በራሱ ሲያከብር እንጂ

በምንም መልኩ የአላህን ብዙነት ለማመልከት አይደለም:: የፍጡራንን ባሕሪያት ለአላህ መገለጫነት መጠቀም ከባእድ አምልኮ ተግባር ይመደባል:: በተመሳሳይ መልኩም ለአላህ ብቻ የሚገቡት ባሕሪያትን ለፍጡራን መገለጫነት ማዋልም እንዲሁ ከባእድ አምልኮ ይቆጠራል::

ለምሳሌ:- ከአላህ ውጭ ያለ ማንኛውም ነገር የሁሉን አዋቂነትና የልዕለ-ኃያልነት ሥልጣን አለው ብሎ ማመን አላህን እንደ ማጋራት ይቆጠራል::

"የግርማና የመከበር ባለቤት የሆነው ጌታህ ስም ተባረከ::" /ቁርዓን 55:78/

3. ስድስቱ የእስልምና እምነት መሠረቶች

አንድ ሰው ሙስሊም ተደርጎ እንዲወሰድ ያለምንም ጥርጥር ሊያምንባቸው የሚገቡ የተወሰኑ መሠረታዊ ጉዳዮች አሉ:: እነዚህም የእምነት መሠረቶች:-

ሀ. በአላህ ማመን

ለ. በመላእክት ማመን

ሐ. አላህ ባወረዳቸው መጽሐፍቶች ማመን

መ. በነቢያትና በመልዕክተኞቹ ማመን

ሠ. በመጨረሻው /በፍርዱ/ ቀን ማመንና

ረ. በመለኮታዊ ፍርዱና ውሳኔው ማመን ናቸው::

ሀ. በአላህ ማመን

አላህ አጋር የሌለው ብቸኛ፣ የፍጡራን ሁሉ ባለቤትና በሁሉ ነገር ልዩ መሆኑ ኢስላም ከአላህ ባሕሪያት ውስጥ ይበልጥ

ትኩረት የሚሰጣቸው ናቸው:: እጅግ በጣም መልካም ሠሪ የሆነው አላህ ብቻ ነው ሊመለክ የሚገባው::

ለ. በመላዕክቱ ማመን

መላዕክት የአላህ ፍጡሮች ናቸው:: ሁሉም ነገር ከሌለበት ያስገኘው አላህ መላዕክትን የፈጠራቸው ከብርሃን ሲሆን ብርቱና ሁሌም አላህ ያዘዛቸውን ብቻ የሚሠሩ ናቸው::

አላህ የአንዳንድ መላዕክትን ስምና ተግባር በቁርዓን ገልፆልናል:: ሙስሊም የሆነ ሰው በመላዕክት መኖር ሊያምን የግድ ነው:: በቁርዓን ከተገለፁት መላዕክት መካከል ጂብሪልና ሚካኢል ይገኙበታል:: ለምሳሌ:- የአላህን ራዕይ ለነቢያትና ለመልዕክተኞች የማድረሱ ተግባር የጅብሪል ነው::

ሐ. በመጻሕፍቱ ማመን

ሙስሊሞች ለነቢያት በወረዱና በሰው ልጅ ባልተበረዙ መመሪያዎች ሁሉ ያምናሉ:: አላህ በቁርዓኑ ውስጥ በጠቀሳቸው ለነቢያት የተሰጡ መጽሐፍት የማመን ግዴታ አለባቸው:: ምክንያቱም ከመበረዛቸው በፊት ትክክለኛ የሱ ቃል የነበሩ ናቸው:: አላህ በቁርዓኑ የጠቀሳቸው የነቢያት መመሪያዎች:-

1. ለኢብራሂም የወረዱት መልዕክቶች
2. ለሙሳ የወረደውና ከመበረዙ በፊት የነበረው ኦሪት /ተውራት/
3. ለዳውድ የወረደውና ከመበረዙ በፊት የነበረው መዝሙረ ዳዊት /ዘቡር/

4. ለዒሳ የወረደውና ከመበረዙ በፊት የነበረው ወንጌል[4] (ኢንጂል)ና
5. ለሙሀመድ የወረደውና እስካሁን ሳይበረዝ በወረደበት መልኩ የሚገኘው ቁርዓን ናቸው::

ሙስሊሞች ከቁርዓን በፊት ወርደው አሁን በተለያዩ እትሞችና ቅጂዎች በመሰራጨት ላይ ያሉት የነቢያት መመሪያዎች በወረዱበት ሁኔታ ላይ ናቸው ብለው አይቀበሉም:: ለመጨረሻ ጊዜ አላህ ባወረደው ቁርዓን እንደተገለፀው ሰዎች ዓለማዊ ፍላጎታቸውን ለማሳካት ብለው በርዘዋቸዋል:: እነዚህ ብረዛዎች በተለያዩ መንገዶች የተካሄዱ ናቸው:: ከነዚህም በመጀመሪያው የሌሉ መልዕክቶችን መጨመር ወይም የነበሩ መልዕክቶችን ማውጣት፣ በመጀመሪያው ይዘውት የነበረውን ትርጉም እንዲፋለስ ማድረግ፣ እንዲሁም በወረዱበት ቋንቋ እንዳይገኙ ማድረግ ናቸው:: እነዚህ ብረዛዎችና ቅየጣዎች ከጊዜ ብዛት ተለምደው ልክ እንደ አላህ ቃል ተወስደዋል:: በአሁኑ ጊዜ ከቁርዓን ውጭ ያሉት መጽሐፍት የአላህ ቃልና የሰዎች ሃሳብ የተደባለቁባቸው ናቸው:: በሰው ልጅ ንክኪና ብረዛ የተነሳ የተዛባ መልዕክት ይዘው ይገኛሉ:: ሙስሊሞች የቀድሞዎቹን መለኮታዊ መጽሐፍት የሚቀበሉ ቢሆንም ለተለያዩ ጉዳዮችና ችግሮቻቸውን የማስሪያ መፍትሄ የሚያደርጉትና ወደ ቅን መንገድ ለመመራት

[4] አሁን በእጃችን በሚገኘው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉት የተለያዩ ወንጌሎች ከኢየሱስ ማረግ በኋላ በሌሎች ፀሐፊዎች የተጻፉ ናቸው:: በቁርዓን ውስጥ የሚጠቀሰው ወንጌል በቀጥታ በመርየም ልጅ ዒሳ (ዐ.ሰ) ላይ የወረደውን እንጂ ከኢየሱስ ማረግ በኋላ በተለያዩ ፀሐፊዎች የተፃፈውን አይደለም::

በምንጭነት የሚጠቀሙት ቁርዓንንና የነቢዩ ሙሀመድ ተምሳሌታዊ አኗኗርን ነው።

መ. በነቢያትና በመልዕክተኞቹ ማመን

ነቢያት መልዕክተኞች ከአላህ መልዕክት ተቀብለው ወደ ህዝባቸው የሚያስተላልፉ በአላህ የተላኩ ሰዎች ናቸው። የተላኩበት ዓላማም የሰው ልጅን አንድ አላህ ወደሚመለክበት ትክክለኛ የእምነት ጎዳና ለመመለስ፣ የሰው ልጅ አላህን እንዴት መገዛት እንዳለበት ለማስተማርና የመድህን መንገድ ለማመላከት ነበር። የትኞቹም ነቢያትና መልዕክተኞች ከአላህ መለኮታዊ ሥልጣን ቅንጣት ታህልም የተጋሩ አልነበሩም። ምንም መለኮታዊ ኃይል የሌላቸው ሰዎችም ነበሩ። አንድ ሙስሊም ሊያመልካቸውም ሆነ ወደ አላህ መቃረቢያ አድርጎ ሊወስዳቸው በፍፁም አይፈቀድለትም። እንዲሁም ደግሞ የጌታ እዝነትና ይቅርታ በነሱ በኩል ወይም እነሱ ራሳቸውን መጠየቅ አይችልም። ስለዚህ "ሙሀመዳዊያን" የሚለው መጠሪያ ለሙስሊሞች የማይገባ ስድብ ነው። እያንዳንዱ ነቢይና መልዕክተኛ እንደነዚህ ዓይነት ተግባራት ሁሉ ከባዕድ አምልኮ የሚመደቡ መሆኑንና የሚተገብራቸው ማንኛውም ሰው ከሙስሊሞች እንደማይቆጠር አስተምሯል።

መልካም ለጋሽ የሆነው አላህ በዓለም በመላ ለሚገኙ ህዝቦች ብዙ ነቢያትን ለዘመናት ልኳል። ሙስሊም የሆነ ሰው በነዚህ በአላህ በተላኩት ነቢያትና መልዕክተኞች ሁሉ ማመን አለበት።

አንዳንዶቹም አላህ በቁርዓኑ ጠቅሷቸዋል:: በስም ከተጠቀሱት[5] መካከል:- አደም /አዳም/፣ ኑህ /ኖህ/፣ ኢብራሂም /አብረሃም/፣ ሙሳ /ሙሴ/፣ ዒሳ /ኢየሱስ/ እና ሙሀመድ (በሁላቸውም ላይ ሰላም ይውረድ) ይገኙባቸዋል ::

ሁሉም የአላህ ነቢያትና መልዕክተኞች ይዘውት የመጡት ኢስላማዊ አስተምህሮት ነበር:: በታሪክ ውስጥ ለአላህ ፍላጎት ያደሩትና በጊዜያቸው ለነበሩት ነቢያትና መልዕክተኞች የወረዱ መመሪያዎችን የተገበሩት ህዝቦች ሁሉ ሙስሊም ይባላሉ:: የአብረሃም ተከታይ የነበሩት ሰዎች ያንን የተከታይነት ስያሜ ያገኙት የአብረሃምን አንድ አምላክን ብቻ የማምለክ እምነት አጥብቀው በመያዝና ራሳቸውን ለአላህ በማስገዛት እንጂ በዘር ሐረግ አልነበረም:: ሙሳም መጥቶ ነቢይነቱን ሲያውጅ አንድ አላህን ብቻ በማምለክ ከልብ ተከትለውት የነበሩ ሁሉ ሙስሊሞች ነበሩ:: እንዲሁም ደግሞ ዒሳ የማያሻሙ ምልክቶችና ተአምራት በመሳየት ነብይነቱን ሲያውጅ በጊዜው የነበሩ ሰዎች ሁሉ ሙስሊም ተብለው እንዲጠሩ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ነቢይነቱን መቀበል ግዴታቸው ነበር:: ዒሳን የተቃወሙ ሁሉ ነቢይነቱንና ትክክለኛውን የእምነት መንገዱን ባለመቀበላቸው ኢስላምን ያልተቀበሉ ሆኑ:: ከአላህ መልዕክተኞች የትኞቹንም መቃወም

[5] በቁርዓን ውስጥ የተጠቀሱት የአላህ መልዕክተኞች:- አደም፣ ኢድሪስ፣ ኑህ፣ ሳሊህ፣ ኢብራሂም፣ ሎጥ፣ ኢስማዒል፣ ኢስሐቅ፣ ያዕቁብ፣ ዩሱፍ፣ ሹዔይብ፣አዩብ፣ ሙሳ፣ ሃሩን፣ ዙልኪፍል፣ ዳውድ፣ ሱሌይማን፣ ኢልያስ፣ የሰዕ፣ ዩኑስ፣ ዘከሪያ፣ ያህያ፣ ዒሳና ሙሀመድ (በሁሉም ላይ ሠላም ይውረድ) ናቸው::

ወይም መጥላት ከኢስላም ያስወጣል::[6] ሙስሊሞች ምንም አጋር ሳይደረግለት አንድ ፈጣሪን ብቻ እንዲመለክ የሰበኩ የአላህ ነቢያትና መልዕክተኞችን ሁሉ መውደድ ይጠበቅባቸዋል:: ነቢያትና መልዕክተኞች ሁሉ ሙሉ በሙሉ ለአላህ ያደሩ ነበሩ፣ በሌላ አገላለፅ ሙስሊሞች ነበሩ::

ሁሉም ነቢያት ከአደም ጀምሮ እስከ ሙሀመድ ያሉት በእምነት የተዛመዱ ወንድማማቾች ነበሩ:: ሁላቸውም ሰዎችን እንዲመሩና እንዲያስተዳድሩ በተለያዩ ጊዜያት ከተለያዩ ሕግጋት ጋር በአላህ ቢላኩም የአስተምህሮታቸው ጭብጥ (ዓላማ) ተመሳሳይ ነበር:: ሁሉም ያስተምሩ የነበረው ሰዎች ፍጡርን ከማምለክ አባዜ ተላቀው ልዕለ-ኃይሉ ፈጣሪን በማምለክ ላይ እንዲፀኑ ነበር:: በኢስላም ነቢዩ ሙሀመድ የመጨራሻው የአላህ መልዕክተኛና የነቢያት መደምደሚያ በመሆናቸው ከሌሎች ነቢያትና መልዕክተኞች ብልጫ አላቸው:: ለዚህ ምክንያቱ:-

1) አላህ ለሰው ልጅ ያወርድ የነበረው ራዕይ (ወሕይ) በርሳቸው ነቢይነት በማብቃቱና ራዕዮችን (ወሕዩችን) በተሟላ መልኩ በቁርዓን ውስጥ በማስቀመጡና
2) የመጨረሻው ነቢይና መልዕክተኛ የሆኑት ሙሀመድ ሁሉም ትውልዶች ሊከተሉትና ሊተገብሩት የሚችሉት አርአያነት ያለው ሕይወት በ23 ዓመት የነቢይነት ዘመናቸው በመምራታቸው ነው::

---

[6] አላህ በነቢዩ ሙሀመድ (ሰ.ዐ.ወ) ላይ የሚከተለውን የቁርዓን አንቀጽ አውርዷል:: *"ለናንተ ከኃይማኖት ያንን በርሱ ኑሁን ያዘዘበትን ደነገገላችሁ፣ ያንንም ወዳንተ ያወረድነውን ያንንም በርሱ ኢብራሂምን፣ ሙሳንና ዒሳንም ያዘዝንበትን፣ ኃይማኖትን በትክክል አቋቁሙ፣ በርሱም አትለያዩ፣ ማለትን (ደነገግን)" /ቁርዓን 42:13/*

አላህ በቁርዓኑ "ከርሱ (ከሙሀመድ) በኋላ ምንም ነብይ ወይም መልዕክተኛ አይመጣም" ብሏል:: ሙሀመድ የነቢያት መደምደሚያ ተብለው የተጠሩትም በዚህ ምክንያት ነው::[7] ይህም ማለት በወሕይ የወረዱትና በነቢዩ ህይወት እና አስተምህሮት የተካተቱት መለኮታዊ ህግጋት ለሰው ዘር በሙሉ እስከ መጨረሻው ቀን ድረስ እንዲያገለግሉ ታስቦ የተቀመሩ ናቸው ማለት ነው:: እውነተኛ አማኝ ለመሆን በሙሀመድ ነብይነት እና በወረደላቸው ወሕይ በማመን እንዲሁም ከእሳቸው በፊት አላህ በላካቸው ነቢያት እና መልዕክተኞች በማመን እና በመታገዝ እራስን ፍፁምና ኃያል ለሆነው አላህ ፍላጎት ማስገዛት አለብን::

ሙስሊሞች በሁሉም ነቢያት እና መልዕክተኞች ቢያምኑም የበለጠ ፋናቸውን የሚከተሉት እና ሙሉ በሙሉ የሚተገብሩት የመጨረሻው መልዕክተኛ (የሙሀመድ) ትምህርቶች እና ምሳሌያዊ ህይወትን ነው:: እጅግ የተከበረው አላህ ስለ ሙሀመድ ሲገልፅ:-

*"(ሙሀመድ ሆይ) ለዓለማትም እዝነት አድርገን እንጂ አልላክንህም::" /ቁርዓን 21:107/ ይላል::*

*ሠ.* **በፍርዱ ቀን ማመን**

ሙስሊም የሆነ ሰው ወደፊት የፍርዱ ቀን እንደሚመጣ እና አላህ በገደብ የለሽ ሥልጣኑ ስጋና ደማችንን አዋህዶ በመቀስቀስ እንደሚሰበስበን ያለአንዳች ጥርጣሬ ማመን አለበት:: አላህ መጀመሪያም ከሌለንበት እንዳስገኘን ሁሉ ወደፊትም በህይወት

---

*[7] አንዳንድ ሙስሊሞች የሚከተሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ አንቀጾች የነብዩ ሙሀመድ መምጣትን የሚተነብዩ አንቀጾች ናቸው ብለው ይጠቅሷቸዋል:-*

*ኦሪት ዘዳግም 18:15 18:18፣ ዮሐንስ 1:19-21 14:16 14:17 15:26 16:7-8 16:12-13::*

ዘመናችንም ለሠራነው ሁሉ በእሱ ፊት ትክክለኛ ፍርድ እናገኝ ዘንድ ከሞት ቀስቅሶ ይሰበስበናል:: ከፍርዱ በኋላ ሞት የሚባል ነገር ሳናይ ለዘለዓለም እንኖራለን:: የፍርዱ ቀን እያንዳንዱ ሰው ወደ አላህ ፊት የሚቀርብበት እና እያንዳንዱ ግለሰብ ስለሥራው የሚጠየቅበት ቀን ነው:: በዚያ ወሳኝ ቀን እያንዳንዳችን በዚህች የህይወት ጎዞአችን የከወንናቸው ጥቃቅን ጉዳዮች (ጥሩም ይሁኑ መጥፎ) እንኳን ሳይቀሩ ተመዝግበው ይቀርቡልናል:: በዚያ ቀን መዋሸትና ማታለል የሚባል ነገር በፍፁም አይታሰብም:: ለበጎ ሥራ ምንዳው ገነት ሲሆን ለክፉ ደግሞ ገሃነም ነው::

ገነት እና ገሃነብ በምናብ የተፈጠሩ ሳይሆኑ በእውን የሚገኙ ትክክለኛ ቦታዎች ናቸው:: ሁሉን አዋቂ እና የመልካም ተግባር ተገቢውን ምንዳ ከፋይ የሆነው አላህ ጀነት ፍፁም ደስታ የሞላበት፣ እጅግ አስደናቂና ዘላለማዊ በሆኑ ጥሩ ነገሮች የተሞላ እና ከስሩ ወንዞች የሚፈሱበት መሆኑን ገልጿል:: በጀነት ሙቀትም ይሁን ቅዝቃዜ፣ ድካምም ይሁን በሽታ ብቻ መጥፎ የምንለው ማንኛውም ዓይነት ነገር የለም:: የደህንነት ባለቤት የሆነው አላህ ማንኛውም ዓይነት በሽታ ከጀነት ነዋሪዎች ላይ ከማንሳቱም በላይ ፍላጎታቸውን ሁሉ እንደሚያሟላላቸው ቃል ገብቷል:: ጀነት ለሚገቡ ሰዎች "ይህን ጀነት ያገኛችሁት በአላህ እዝነት እና በመልካም ተግባራችሁ ምክንያት ነው" ይባላሉ:: በዚያ ቀን የሙእሚኖች ትልቁ ደስታ የትልቆች ትልቅ የሆነውን አላህ ፊት ለማየት መብቃታቸውን ነው:: አንድ ሰው ሙስሊም ሆኖ (እራሱን ለአንድ አላህ አስገዝቶ) እስካልሞተ ድረስ ሙስሊም ሆኖ መወለዱ ወይም መኖሩ ብቻ ለጀነት አያበቃውም::

ሁሉን አዋቂው አላህ ገሃነብ ደግሞ ሊያስገቡት ከሚችሉት በላይ አስቃቂ የሆነ ቦታ እና ማቀጣጠያው ሰው እና ድንጋይ የሆነ እሳት መሆኑን ይገልፃል:: ጥብቅ እና ብርቱ የሆኑ መላዕክት ሰዎችን ወደ ገሃነብ ሲጨምሩ *"ከዚያም ይህ ያ በእርሱ ታስተባብሉበት የነበራችሁት ነው . . . ::" /ቁርዓን 83:17/* ይላሉ::

አላህ ለታዘዙት እጅግ አዛኝ እና እጅግ ርህሩህ ቢሆንም እሱን መገዛት አሻፈረኝ ባሉት ላይ የሚያሳርፈው ቅጣት የበረታ ነው::

የአላህ ወደር አልባ ፍትህ የተለየ እና ፍፁም ነው:: በፍርዱ ቀን ሁሉም ሥራዎች ይቀርባሉ፣ እያንዳንዱ ሰውም እንደየሥራው ፍትሃዊ ብያኔ ያገኛል:: የአላህ እዝነት ካልታከለበት ምንም ያህል መልካም ሥራ ቢኖረን ለጀነት የሚያበቃን አይሆንም::

## ረ. በመለኮታዊው ውሳኔ (ቀደር) ማመን

የአላህ እውቀት በጊዜ የማይገደብ በመሆኑ በፍጡሩ ላይ የሚከሰተውን እያንዳንዱን ነገር ያውቃል:: ይህም ማለት ሁሉንም ጠባቂ የሆነው አላህ ያለፉ፣ አሁን በመካሄድ ላይ ያሉና ወደፊት የሚከሰቱ ድርጊቶች ሁሉ ያውቃል ማለት ነው:: የአላህ መለኮታዊ እውቀት ፍፁም ነውና:: አላህ ሁሉን አዋቂ ከመሆኑም ባሻገር የሚሆነው እሱ እንዲሆን ያሻው ነገር ብቻ ነው::

ሁሉን በቁጥጥሩ ሥር አድራጊው አላህ በፍጡራኑ ላይ ያለው ልእልና ፍፁም ነው:: እያንዳንዱ ነገርና ክስተት የእሱ ፍቃድና ውጤቶች ናቸው:: ያለ እሱ ሥልጣን፣ ፍላጎት እና እውቀት ሊገኝ የሚችል አንድም ነገር የለም::

### 4. የሰው ልጅ የፈለገውን መርጦ የማድረግ መብቱ

ለሰው ልጅ ጥሩ ወይም መጥፎ የመምረጥ ሙሉ መብት ከከባድ ኃላፊነት ጋር ማጎናፀፉ የኢስላም ልዩ ባህሪይ ነው:: አላህ ለሰው ልጅ በሰጠው በዚህ ልዩ መብት የሰውን ልጅ አክብሮታል:: ይሁን እንጂ መብቱ ተጠያቂነትንም ጭምር ያዘለ በመሆኑ በፍርዱ ቀን ለምን ዓላማ እና ተግባር እንደተጠቀመበት ይጠይቀዋል::

ይህ ለሰው ልጅ የተሰጠው የመምረጥ ነፃነት አላህ በፍጡራኑ ላይ የሚከሰተውን እያንዳንዱን ነገር ያውቃል ከሚለው ሃሳብ ጋር በምንም መልኩ አይቃረንም:: እዚህ ላይ "አላህ ነገ ኃጢያት እንደምንሠራ የሚያውቅ እስከሆነ ኃጢያቱን ከመሥራት የመታቀብ ምንም እድል የለኝም:: ምክንያቱም የአላህ እውቀት እንከን የለሽ እና ተግባራዊ ከመሆን የሚመልሰው ኃይል የለም ተብሏልና" የሚል ሃሳብ ሊነሳ ይችላል:: ማንም ሰው ምን እንደሚወስን አላህ አስቀድሞ ያውቃል ማለት ሰውየው የሚወስነውን ውሳኔ ሁሉ እንዲፈፅም ያስገድደዋል ማለት አይደለም:: አንድ ሰው ጥሩ አልያም መጥፎ ውሳኔ ሊወስን ይችላል:: ሆኖም ውሳኔውን ተግባራዊ የማድረግ ወይም የመተው ሙሉ መብት የግለሰቡ ነው::

የሰው ልጅ የፍላጎቱን የመምረጥ ነፃነት አላህ በፍጡራት ላይ ያለውን የልዕለ-ኃያልነት ሥልጣንም የሚጋፋ አይደለም:: እንዲሁም ያለ አላህ ፍቃድ በፍጡራት ላይ ማንኛውም ነገር አይከሰትም የሚለውን ሃሳብም አይቃረንም::

አንድ ሰው የመምረጥ ነፃነት የሚባለው ነገር ሊሆን የማይችል እንደሆነ አድርጎ ሊያስብ ይችላል:: አንድ ነገር ልብ ልንል ይገባል፤ አላህ ለእያንዳንዳችን የፍላጎት አቅጣጫ የመተለምና ትልማችንን የመተግበር ችሎታ የሰጠን በመሆኑ አላህ የምርጫችንን የምንሠራ አድርጎ ፈጥሮናል:: አንድ ሰው የምርጫውን ሲሠራ አላህ የሰውየውን ፍላጎት እንዲፈፅም የሚያስፈልጉትን ነገሮች እና ሁኔታዎች በመለኮታዊ ችሎታው ያሟላለታል:: የሰው ልጅ የፍላጎቱን የመምረጥ ነፃነት ያገኘው በአላህ ፍላጎት ነው:: አላህ ሰዎች የሚያሳልፉት ውሳኔ ብቻ ሳይሆን የራሳቸውን የመምረጥ ነፃነት ተጠቅመው ይህንን ውሳኔ ለመወሰን እንዲችሉ ብቃቱን ሰጥቷቸዋል:: ለምሳሌ:- አንድ ሰው ጥሩ ነገር ለመሥራት ያስባል:: ሆኖም ለመሥራት አስቦት የነበረውን ጥሩ ነገር ሳይተገብረው ይቀራል:: ያ ሰውዬ በተግባር ባያውለውም ጥሩ ነገር ለመሥራት አስቦ ስለነበር ብቻ ከአላህ

ምንዳ ያገኛል:: ቢተገብረው ደግሞ አላህ ለበጎ ሃሳቡም ለበጎ ተግባሩም ምንዳ ይከፍለዋል:: አላህ በአንድ በኩል ጥሩ ነገር ለመሥራት ስለታሰበ ብቻ ምንዳ ሲከፍል በሌላ በኩል ግን መጥፎ ተግባር ለመፈፀም ታስቦ ሳይተገበር ቢቀር አይቀጣም::

## 5. በኃይማኖት ማስገደድ የለም

አንድ ሰው ሙስሊም ሊሆን የሚችለው በፍላጎቱ ሙስሊም መሆንን ሲመርጥ ብቻ ነው:: የሰው ልጅ የተፈጠረበት ዓላማ በገዛ ፍላጎቱ አላህን ይገዛ ዘንድ ነው:: ስለዚህ ማንኛውም የእምነት ድርጊት ዋጋ ሊኖረው የሚችለው የሰው ልጅ የመምረጥ ነፃነቱን ተጠቅሞ በመቀበል ሲፈፅመው ብቻ ነው:: አንድ ሰው ማንኛውም እምነት ተገዶ እንዲቀበል ቢደረግ እምነቱ የይስሙላና ፍሬ ቢስ ይሆናል:: ደጉ አላህ "በኃይማኖት ማስገደድ የለም፣ ቅኑ መንገድ ከጠማማው በእርግጥ ተገለጠ፣ በጣዖትም የሚክድና በአላህ የሚያምን ሰው፣ ለርሷ መበጠስ የሌላትን ጠንክራ ዘለበት በእርግጥ ጨበጠ፣ አላህ ሰሚ አዋቂ ነው::" /ቁርዓን 2:256/ ብሏል::

## 6. አምስቱ የኢስላም ማዕዘናት

ማንኛውም ሙስሊም በኃላፊነት ተቀብሎ የግድ ሊተገብራቸው የሚገቡ አምስት የአምልኮ ተግባራት አሉ:: እነዚህን የአምልኮ ተግባራት አለማከናወን ከወንጀሎች ሁሉ የከፋው ነው:: የኢስላም ውብ እና ብርቅዬ ህንፃ የተገነባው

በእነዚህ መሠረቶች ላይ ነውና:: ማንም ሰው የእነዚህ ተግባራት ግዴታነት ካስተባበለ ሙስሊም ተደርጎ አይወሰድም::

በኢስላም እምነት የግድ መተግበር ያለባቸው አምስቱ ተግባራት:-

ሀ. ሸሃዳ:- ከአላህ በስተቀር ሊገዙት የሚገባ ጌታ የለም፣ ሙሀመድም መልዕክተኛው ናቸው በማለት እምነትን ማረጋገጥ

ለ. ሰላት:- በቀን አምስት ጊዜ መስገድ

ሐ. ዘካ - ከተቀማጭ ሃብት በየዓመቱ የድሆችን ድርሻ መክፈል

መ. ሶውም:- በየዓመቱ ረመዳን ወርን መፆም እና

ሠ. ሐጅ:- አቅሙ ካለ በህይወት ዘመን አንድ ጊዜ ወደ መካ መንፈሳዊ ጉዞ ማድረግ ናቸው::

## ሀ. ሸሀዳ (እምነትን በቃል ማረጋገጥ)

ማንም ሰው የእስልምና እምነትን ሲቀበል "ከአላህ በስተቀር ሊመለክ የሚገባ ጌታ የለም፣ ሙሀመድም የአላህ መልዕክተኛ መሆናቸውን በልቤ አምኜ በቃሌ እመሰክራለሁ" እንዲል የግድ ነው:: በዚህ በጣም ግልጽ፣ የግድ አስፈላጊ እና እጅግ ኃያል በሆነ እወጃ አንድ ሰው ሙስሊም ሊሆን ይችላል:: ይህንን እወጃ በልቡ ተቀብሎ በምላሱ ሊመሰክር ያለምንም አስገዳጅ ኃይል ጣልቃ ገብነት መሆን ይኖርበታል::

ይህንን የእምነት እወጃ ቃል በሶስት አንኳር ክፍሎች በመክፈል ተንትነን ልንመለከተው እንችላለን::

1. *ከአላህ በስተቀር ማንኛውም የአምልኮ ተግባር ለአንድ አላህ ብቻ የሚገባ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው::*[8]
2. *ሊመለክ የሚገባው ጌታ የለም* ባዕድ አምልኮን የሚፃረር እና የሚያፈርስ ቃል ነው::
3. *ሙሀመድ የአላህ መልዕክተኛ ናቸው የሚለው ሰስተኛው* የእምነት እወጃው ክፍል የሙሀመድን የመጨረሻ ነብይነትንና መልዕክተኝነት የሚያረጋግጥ ቃል ነው::[9] ይህም ቁርዓንና ትክክለኛ የነቢዩ ሐዲሶችን መቀበል ያሳያል::

አንድ ሰው ሸሃዳውን በልቡ አምኖ በቃሉ ከመሰከረ የባዕድ አምልኮ ተግባራትን ሁሉ እርግፍ አድርጎ በመተው ዒባዳ ሁሉ ለአላህ ብቻ የሚገባው መሆኑን አረጋገጠ ማለት ነው:: ብጤ ወይም ሸሪክ የሌለው አላህ አንድ ሰው ሸሃዳን ከልቡ አምኖበት ካለው ያለፈው ወንጀሉን (ምንም ያህል የበዛ ቢሆን እንኳን) እንደሚምረው ቃል ገብቷል:: በተጨማሪም ከዚያ በፊት በሠራቸው በጎ ተግባራት ምንዳ ያገኛል::

---

[8] የለም የሚለው አፍራሽ ቃል ከአላህ በቀር ሊመለክ የሚገባው፣ መለኮታዊነት ያለውና ከጌትነት ሥልጣኑ የሚጋራ እንዲሁም በፈጣሪነት ፍጡርን ሊንከባከብ (ደግፎ ሊያቆይ) የሚችል ማንም ፍጡር የለም ማለት ነው::

[9] አንድ ሰው "ኢስላም በሁሉም ነቢያቶች የሚያምን ከሆነ አንድ ሰው የእምነት ቃሉን ሲሰጥ ሌሎች ነቢያቶችን ሳይጠቅስ ነቢዩ ሙሀመድን ብቻ የሚጠቅሰው ለምንድነው? ብሎ ሊጠይቅ ይችላል:: ለዚህ መልሱ ቀላል ነው:: አንድ ሰው የነቢዩ ሙሀመድን (ሰ.ዐ.ወ) ነቢይነት ሲመሰክር ከነቢዩ በፊት ለነበሩት ነቢያቶች ሁሉ እውቅና መስጠቱ ነው:: ለምሳሌ:- አንድ ሰው "ከአላህ በቀር ሌላ አምላክ የለም ሙሳ (ዐ.ሰ.) የአላህ መልዕክተኛ ነው" ብሎ የእምነት ምስክርነት ቃሉን ቢሰጥ ከሙሳ በኋላ በመጡ ነቢያት ማመን አያስፈልገውም::

## ለ. ሰላትን በቀን አምስት ጊዜ መስገድ

በቀን የአምስት ወቅት ሰላቶችን መስገድ በእያንዳንዱ ሙስሊም ላይ ግዴታ ነው። አንድ ሙስሊም እነዚህ ሰላቶችን በሚሰግድበት ጊዜ አንድ አላህን ብቻ ለማምለኪያነት የተገነባው ቤት (ካዕባ) ወደሚገኝበት መካ መቀጣጨት አለበት። ይህ ቤት የተገነባው በኢብራሂም እና በልጃቸው ኢስማኤል ነው።

እዚህ ላይ ኢስላም ምንም ዓይነት ቅዱስ ምልክት እንደሌለው ሊታወቅ ይገባል። የሰላት አቅጣጫችንን ወደ ካዕባ እናደርጋለን ማለት ካዕባን እናመልካለን ማለት አይደለም። የሰላት አቅጣጫ ወደ ካዕባ አድርጎ መስገድ ሙስሊሞች ውበት፣ ሥርዓት እና ወጥነት ባለው መልኩ አምልኮአቸውን እንዲተገብሩ ያደርጋቸዋል። ለካዕባም ሆነ ለማንኛውም ፍጡር የሚገዛ ሰው እንደ ጣኦት አምላኪ ይቆጠራል።

ለካዕባ ግንባታ የዋሉ ቁሳቁሶችም ከሌሎች የግንባታ ቁሳቁሶች የተለየ ቅዱስነት የላቸውም።

እነዚህ የአምስት ወቅት ሰላቶች ከቀን እስከ ሌሊት ባለው ጊዜ የሚሰገዱ ናቸው። ሰላቶቹም ሰጋጁ ሥራውን በተደጋጋሚ እንዲፈትሽና ራሱን ለአላህ ትዕዛዛት እንዲያስገዛ የሚያደርጉት ናቸው። እንዲሁም ሰጋጅንና ፈጣሪን በቀጥታ የሚያገናኙ ጎዳናዎች ናቸው። ሰላቶች አንድ ሰው በአምልኮ ወደ አላህ ከልቡ የሚመለስባቸው፣ ለአላህ ምስጋና የሚያቀርብባቸው፣ የአላህ ምህረትን የሚለምንባቸውና ወደ ቅኑ መንገድ እንዲመራውና እዝነቱን እንዲለግሰው የሚጠይቅባቸው የአላህ መልካም ስጦታዎች ናቸው። አንድ ሙስሊም ብዙ ተጨማሪ ሰላቶችን

በፈቃደኝነት ሊሰግድ ይችላል። ሰላት በጥቅሉ ፀሎት (ዱዓ) ማለት ስለሆነ በማንኛውም ጊዜና ቦታ ሊሰገድ ይቻላል።

### ሐ. ዓመታዊ ዘካዕን መክፈል

በቂ ተቀማጭ ሀብት ያለው ማንኛውም ሙስሊም በየዓመቱ ከሀብቱ የድሆችን ድርሻ የመክፈል ኃይማኖታዊ ግዴታ አለበት። ዘካዕ የአረበኛ ቃል ሲሆን ቀጥተኛ ትርጉሙም ማጥራት ወይም ማፅዳት ማለት ነው። ማንኛውም ነገር የአላህ ሀብት ነው። ገንዘብም ለሰው ልጅ በአደራ መልክ የተሰጠ የአላህ ሃቅ ነው። ከዚያ አላህ በአደራ መልክ ካስቀመጠብን ሀብት ዘካዕ መክፈል ሀብቱ እንዲፀዳ ያደርጋል። ዘካዕ በህብረተሰቡ መካከል ሚዛናዊ የሆነ የሀብት ክፍፍል እንዲኖር ከማድረጉም በላይ ደሃ የህብረተሰብ ክፍሎች ቋሚ እርዳታ የሚያገኙበት መንገድ ነው። ዘካዕ ስስታምነትን በማስወገድ፣ ርህራሄን በማጠናከር እና ቸርነትን በማስፈን የሰጭውን ልብ ያለዝባል።

የዘካዕ መጠን ዓመቱን ሙሉ የተካበተው ሀብት በመቶ ተሰልቶ ሁለት ከግማሹን እጅ ያህል ነው። ዘካዕ የሚሰላው ከተቀመጭ ሂሳብ እንጂ ከገቢ ሂሳብ አይደለም።

### መ. ረመዳን ወርን መፆም /ሰውም/

ለአቅመ አዳም ወይም ለአቅመ ሄዋን የደረሰ/ች ማንኛውም ሙስሊም የረመዳን ወርን የመፆም ግዴታ አለበት። ይህ ወር በኢስላም ትልቅ ቦታ ያለው ወር ነው። ምክንያቱም ለነቢዩ ሙሀመድ ለመጀመሪያ ጊዜ ቁርአን የወረደላቸው በዚህ ወር ነው።

በጨረቃ አቆጣጠር የሚሰላው አንድ ዓመት በፀሐይ አቆጣጠር ከሚሰላው አንድ ዓመት በአስራ አንድ ቀን ስለሚቀንስ

የረመዳን ወር ቀስ በቀስ ሁሉንም የዓመቱን ወቅቶች ያዳርሳል:: ዘካዕ የሀብት ማፅጂያ እንደሆነ ሁሉ ረመዳን የቀልብ ማፅጂያ ነው:: ፆሙም በንጋት ላይ ይጀምርና ሲመሽ ይጠናቀቃል:: ጿሚ የሆነ ሰው ፀሐይ ሳይጠልቅ መብላት፣ መጠጣት እና የግብረስጋ ግንኙነት ማድረግ አይፈቀድለትም::[10] ፆም ራስን መቆጣጠር እና ታጋሽነትን ያስተምራል:: እንደ ሰላት ሁሉ ፆምም በቅን አምልኮ ወደ አላህ የመመለሻ መንገድ ነው::

የሙስሊሞች ክብረ በዓላት ሁለት ናቸው:: አንደኛው በረመዳን መጨረሻ የሚከበረው ኢድ አልፈጥር ሲሆን ሁለተኛው በሃጅ መጨረሻ የሚከበረው ኢድ አልአደሃ ናቸው::

ፆም ድሆች ምን ዓይነት ህይወት እንደሚገፉ እንድንገነዘብ ያደርጋል:: አላህ የለገሰን አንድ ብርጭቆ ውሃ ወይም አንድ ወቅት የምንበላው ምግብ ምን ያህል ደረጃ እንዳለው በማሳወቅ አስፈላጊውን ምስጋና ለአላህ እንድንሰጥ ያደርጋል::

ሠ. ወደ መካ መንፈሳዊ ጎዞ (ሐጅ) ማድረግ

እያንዳንዱ ሙስሊም ጤና እና አስፈላጊውን ወጪ የመሸፈን ብቃት ካለው በህይወት ዘመኑ አንዴ ወደ መካ መንፈሳዊ ጉዞ ማድረግ አለበት:: በመላው ዓለም የሚገኙ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሙስሊሞች አላህን ብቻ ለመገዛትና ለማምለክ በየዓመቱ በመካ ይሰበሰባሉ::

የሐጅ ኃይማኖታዊ ተግባር ለመጀመሪያ ጊዜ የጀመሩት ነቢዩ ኢብራሂም ሲሆኑ እንደገና እንዲጀመር ያደረጉት ነቢዩ ሙሀመድ ናቸው:: ሐጅ ምዕመናን የመጡበትን ማህበረሰብ

---

[10] ኢስላም ሰዎች ክብረ-ንጽህናቸውን እንዲጠብቁ ያዛል:: ከጋብቻ ፊት የሚደረጉ የተቃራኒ ጾታ ግንኙነት ይከለከላል::

በብርቱ እያስቸግሩ የሚገኙት የዘር፣ የኢኮኖሚ እና የማህበራዊ ህይወት እንቅፋቶች ወደ ጎን ትተው ለአንድ ዓላማ በህብረት እንዲቆሙ ያደርጋል። እያንዳንዱ ተጓዥ ታጋሽነትን፣ ከተለያዩ ጎጂ ድርጊቶች መታቀብን እና ርኅሩህነትን እንዲለማመድም ያደርጋል።

ሐጃጆች የሚለብሱት ቀለል ያለ እና አንድ ዓይነት ልብስ ስለሆነ በመካከላቸው የሀብት እና የባህል ልዩነት አይንፀባረቅም። በሐጅ ወቅት የሚካሄዱ የአምልኮ ተግባራት በሙሉ ሐጃጆች ሁሌ አላህን እንዲያስታውሱ ከማድረጋቸውም ባሻገር የሰው ልጅ በሙሉ የመጣው ከአላህ የሚመለሰውም ከአላህ መሆኑን የሚያስገነዝቡ ናቸው።

7. ቁርዓን

ቁርዓን በጂብሪል[11] አማካኝነት በመውረድ የመጨረሻው ነብይ እና መልዕክተኛ በሆኑት ሙሀመድ (ሰ.ዐ.ወ) ልቦና የተቀረፀ የመጨረሻው እንከን የለሽ፣ የማያሻማ እና የተሟላ ትክክለኛ የአላህ ቃል ነው።

በርካታ የነቢዩ ባልደረቦች (ሶሀቦች) ቁርዓንን በትጋት በመማር እና ያለ አንዳች ግድፈት እና ስህተት በቃላቸው በመያዝ ብዙ ዘመናትን ተሻግሮ እኛ ዘንድ እንዲደርስ አድርገዋል።

[11] በኢስላም የቅዱስ መንፈስ እየተባለ የሚጠራው መልዓኩ ጅብሪል ነው። ጅብሪልን ማምለክ በፍጹም የተከለከለ ነው። በሌላም በኩል በሥላሤዎች ማመን ከመሠረታዊ የእስላምና እምነት (በአንድ አምላክ ማመን) በግልጽ ይቃረናል።

ከቁርዓን በፊት ለተለያዩ ነቢያት እና መልዕክተኞች መመሪያነት የወረዱ መጽሐፍትም የአላህ ቃሎች ናቸው:: ቁርዓን ግን ከዚያ በፊት የነበሩት የአላህ መጽሀፍት ታድሰው፣ የበለጠ ግልጽ ሆነው እና ተጠቃልለው የቀረቡበት የአላህ ቃል ነው:: ቁርዓን በብዙ መልኩ ሲታይ ከሌሎች በጣም የተለየ ነው::

ሁሉን ጠባቂ የሆነው አላህ ቁርዓንን ከማንኛውም ዓይነት ብረዛ ጠብቆ አቆይቶታል:: ቁርዓን ለሙስሊሞች ብቻ ሳይሆን የኃይማኖት ታሪክ አጥኚ በሆኑት ምሁራንም በዓለም ላይ ከሚገኙ የኃይማኖት መጽሐፍት ሁሉ በወረደበት ትክክለኛ ይዘት የሚገኝ ብቸኛ የኃይማኖት መጽሐፍ መሆኑን ይመሰክራሉ::[12] ሌሎች የኃይማኖት መጽሐፍት ግን ይዘታቸው ላይ ለውጥ ተደርጎበት እና ቋንቋቸው ተቀይሮ ይገኛሉ:: አንዳንዶቹ (ለምሳሌ ለነቢዩ ኢብራሂም ወርዶ የነበረው) እስከነአካቴው ጠፍተዋል:: ሌሎቹ ደግሞ በተደጋጋሚ ተከልሰዋል:: የተወሰኑ መልዕክቶቻቸው ተወግደዋል አሊያም ሲወርዱ ይዘውት የነበረው መልዕክት በሌላ ተተክቷል::

አላህ እንደዚህ ዓይነት ንክኪ ቁርዓን ላይ እንዲደርስ አልፈቀደም:: ምክንያቱም እስከ ፍርዱ ቀን ድረስ ለሰው ልጅ እንዲያገለግል ነው ያወረደው:: አዲስ ነቢይ ወይም መልዕክተኛ አይላክም:: ቁርዓን በአላህ በራሱ ባይጠበቅ ኖሮ ልክ በወረደበት

[12] ለተጨማሪ መረጃ Joseph Van Ess, "Muhammad and the Qur'an: Prophecy and Revelation" in Christianity and the World Religions: Paths to Dialogue with Islam, Hinduism and Buddhism. Edited by Hans Kung (Garden City, NY: Double Day and Co., 1986); and Michael Sells, Approaching the Qur'an: The Early Revelations (Ashland, OR: With Cloud Press, 1999) የተሰኙ መጽሐፍትን ይመልከቱ::

ሁኔታ አሁን ልናገኘው አንችልም ነበር። ለዚህም ሲል ነው ቁርዓንን የመጠበቅ ኃላፊነት ለሰው ያልሰጠው።[13]

አላህ ተከታታይ ነቢያትን እና መልዕክተኞች እየላከ ስለነበር ከቁርዓን በፊት የወረዱት መንፈሳዊ መጽሐፍት እንዳይበረዙ መጠበቁ የቁርዓንን ያህል የግድ አስፈላጊ አልነበረም። በመጽሐፍቱ ተካተው የነበሩት ህግጋት እና ትዕዛዛት በተሟላ መልኩ የተቀመጡ አልነበሩም። እናም በየጊዜው እየተሻሻሉ እና እየተቀያየሩ መጥተዋል። ለምሳሌ:- ዒሳ በአላህ ትእዛዝ ቀድሞ ክልክል የነበሩ ተግባራትን አንድ ፈጣሪ የሚመለክበት ሥርዓት በማያዛንፍ መልኩ ፈቅደዋል።

ቁርዓን ሌላው አስደናቂ ገፅታው የራሱና በውስጡ የተካተቱ መልዕክቶች ተአምራዊነት ነው።

ሁሉም ነቢያትና መልዕክተኞች የነቢይነታቸውን እውነትነት ማረጋገጫ ይሆናቸው ዘንድ ከአላህ ታአምራት ይሰጣቸዋል። ኢብራሂም ከሚንቀለቀል እሳት ላይ ተጥለው ያለአንዳች ጉዳት ተርፈዋል። ሙሳም በአላህ እዝነት በዘንጋቸው ባህርን ለመክፈል ችለዋል። የመርየም ልጅ ዒሳም ሙታንን እና በሽተኞችን በመንካት በአላህ ፍቃድ ነፍስ እንዲዘሩ አድርገዋል፣ ወደ ጤንነት መልሰዋል። የእነዚህ ሁሉ ታአምራት ዓላማ ነቢይነታቸውን እና መልእክተኛነታቸውን ለማረጋገጥ ነበር። ነገር

---

[13] ቁርዓን አንድ መቶ አሥራ አራት ምዕራፎችን የያዘ አንድ "መጽሐፍ" ነው። ይህም በአሁኑ ጊዜ በተለያዩ ቅጂዎች ተጽፎ ከሚገኘው "መጽሐፍ ቅዱስ" ልዩ ያደርገዋል። የፕሮቴስታንት ክርስቲያኖች "መጽሐፍ ቅዱስ" ቅጂ 66 መጽሐፍት የያዘ ሲሆን የሮማ ካቶሊክ ክርስቲያኖች "መጽሐፍ ቅዱስ" ቅጂ ወደ 72 መጽሐፍት የተካተቱበት ነው። ከዚህም በላይ መጽሐፍቶች የተካተቱበት "መጽሐፍ ቅዱስ" ይገኛል።

ግን ስለ ተአምራቶቹ እማኝ መሆን የሚችሉት በዘመኑ የነበሩ ሰዎች ብቻ ናቸው:: የሙሀመድ ነቢይነት በተመሳሳይ መልኩ በብዙ ተአምራት የታጀበ ነበር:: ከነዚያም መካከል በጣም ትልቁና ዋነኛው ቁርዓን ነው:: አላህ ቁርዓን ትክክለኛ የሱ ቃል ስለመሆኑ ጥርጣሬ ያላቸው ሰዎች ከቁርዓን ተመሳሳይነት ያለው አንድ አጭር ሱራ እንኳን እንዲያቀርቡ ለፉክክር ጋብዟል:: /እዚህ ላይ የቁርዓን አጭሩ ምዕራፍ ሦስት አንቀጾች ብቻ ያለው መሆኑን መግለጹ አስፈላጊ ይመስለኛል::/ ቁርዓንን ዝም ብሎ ማናናቅና እስልምናን በጭፍን ማጥላላት የሚቀናቸው በርካታ ሰዎች በታሪክ የነበሩና አሁንም ያሉ ቢሆንም ይህንን ማድረግ ህልም ሆኖባቸዋል:: የፉክክር ግብዣው እስከ ቂያማ ቀን ድረስ የሚቆይ ነው::

በሥነ-ጽሑፋዊ ገጽታው እጅግ በጣም የረቀቀ መሆኑ ሌላው የቁርዓንን ተአምራዊነት ማሳያ ነው:: በዐረብኛ ሥነ-ጽሑፍ ታሪክ ከታዩት ዝርወ-ጽሑፎች ሁሉ እጅግ መሳጩና ልብ ነኪው ቁርዓን ነው:: በቁርዓን የሚስተዋለው ምጡቅ የአቀራረብና የአገላለጽ ዘዴም ሊያስመስሉት ፈፅሞ የማይቻልና በዐረብኛ ሥነ-ጽሑፍ ታሪክ ያልተከሰተ ነው:: ቁርዓን በወረደበት አኳሀን ህያው በሆነ የዐረብኛ ቋንቋ በቢሊዮን ለሚቆጠሩ ሕዝቦች እያገለገለ የሚገኝና በዓለም ለሚገኝ መላው የሰው ዘር የወረደ የአላህ ቃል ነው:: አሁን በአገልግሎት ላይ የሚገኙት አብዛኞቹ ኃይማኖታዊ መጻሕፍት የመጀመሪያ ጽሑፋቸው ከመጥፋቱም ባሻገር በመጀመሪያ የተጻፉበት ቋንቋ አሁን አገልግሎት ላይ የማይውል ናቸው::

በቁርዓን ውስጥ ከአላህ ቃል ውጭ አንድም የነቢዩ ሙሀመድ ቃል አይገኝም:: በህይወት ዘመናቸው ነቢዩ ማንበብና መጻፍ የማይችሉ ነበሩ:: ቁርዓን በጂብሪል አማካይነት ሲወርድላቸውም በትክክል እንደ አወራረዱ ለባልደረቦቻቸው ያጽፉ ነበር:: ባልደረቦቻቸውም ከእሳቸው ዘመን ጀምሮ ቁርዓንን በጽሑፍና በቃል መዝግበው አስቀምጠዋል::

ቁርዓን በዘመናችን ከሚገኙት የኃይማኖት መጽሐፍት ውስጥ ያልተበረዘ ብቸኛው የአላህ ቃል ነው:: ቁርዓን ሁለት ሦስት ቅጂ የለውም:: ብዙ የቁርዓን ትርጉሞች ቢኖሩም በምንም መልኩ ከዐረብኛው ጋር አይመጣጠኑም:: ቀጥሎ የቁርዓን 112ኛ ውን ሱራ ፍቺ /የዐረብኛውን ትርጉም/ በናሙናነት አቅርበናል::

*"በል:- እርሱ አላህ አንድ ነው:: /የሁሉ/ መጠጊያ ነው:: አልወለደም፣ አልተወለደምም:: ለርሱም አንድም ብጤ የለውም::" /ቁርዓን 112:1-4/*

## 8. ነቢዩ ሙሀመድና ሱናቸው

ነቢዩ ሙሀመድ /ሰ.ዐ.ወ/ እንደ አውሮፖ አቆጣጠር በ570 ከተከበሩት ሁለት ነቢያት ከኢብራሂምና ከበኩር ልጃቸው ኢስማዒል የዘር ሐረግ ተወለዱ:: በልጅነታቸው "ታማኙ" በሚል ቅጽል ስም ይታወቁ ነበር:: አርባ አመት ሲሞላቸው አላህ የመጨረሻው ነቢዩና መልዕክተኛው እንዲሆኑ መረጣቸው ::

ሱና የሚለው ቃል የሚያሳየው የነቢዩን ንግግሮችን እና ድርጊቶች እንዲሁም ሌሎች ሰዎች ሲሰሩዋቸው አይተው በዝምታ ያለፏቸው ተግባራትን ነው:: ሃዲሶች እውቅ በሆኑ መጽሐፍት ተሰብስበው ይገኛሉ:: እንደ ቁርዓን ሁሉ ሱናም የአላህ ወህይ ውጤት ነው:: ከቁርዓን የሚለየው ቀጥተኛ የአላህ ቃል ባለመሆኑ

ነው:: እውቀቱ ከአላህ የሆነ መለኮታዊ ራኢይ ሲሆን ቃሉ ግን ከነቢዩ የተገኘ ነው:: ሱናም በጥንቃቄ ተጠብቆ ከትውልድ ወደ ትውልድ ተላልፏል::

የነቢዩን ሱና መከተል በእያንዳንዱ ሙስሊም ላይ ግዴታ ነው:: አላህ አማኞች መልዕክተኛውን እንዲከተሉ በቁርዓን አዝዟልና::

*"እናንተ ያመናችሁ ሆይ፤ አላህን ተገዙ፤ መልዕክተኛውንና ከእናንተም የሥልጣን ባለቤቶችን ታዘዙ፤ በማንኛውም ነገር ብትከራከሩ በአላህ እና በመጨረሻው ቀን የምታምኑ ብትሆኑ (የተከራከራችሁበትን ነገር) ወደ አላህ እና ወደ መልዕክተኛው መልሱት፤ ይህ የተሻለ፣ መጨረሻውም ያማረ ነው::" /ቁርዓን 4:59/*

የተፈጠርንበት ዓላማ አላህን በብቸኝነት ለመታዘዝ እና ለመገዛት ነው:: ይህንን ዓላማ በብቃት ለመወጣት ደግሞ የነቢዩ ሙሀመድን (ሰ.ዐ.ወ) አስተምህሮቶችና ተግባራትን መከተል ግድ ይላል:: አላህ:- *"ለእናንተ፣ አላህንና የመጨረሻውን ቀን የሚከጅል ለሆነ ሰው፣ አላህንም በብዙ የሚወሳ፣ በአላህ መልዕክተኛ መልካም መከተል አለባችሁ::" /ቁርዓን 33:21/* ይላል::

ነቢዩ ሙስሊሞች የአምልኮ ተግባራትን ሁሉ እንዴት መፈፀም እንዳለባቸው አሳይተዋል:: ነቢዩ የሞቱት በ63 ዓመታቸው ሲሆን የተቀበሩት በመዲና (የስራብ) ከተማ በመኖሪያ ቤታቸው ውስጥ ነበር::* ሙስሊሞች ለእሳቸው እና ለባልደረቦቻቸው ዘወትር ሰላምታ ያቀርቡላቸዋል:: ሰላምታ ማድረሱ ከሁሉም ሙስሊሞች የሚጠበቅ ተግባር ነው::

* ነቢዩ የተቀበሩት በሞቱበት ቦታ እንደነበር ለማስገንዘብ እንወዳለን

እስልምና በነቢዩ መሰበክ በጀመረ በአንድ ክፍለ ዘመን ውስጥ ብቻ ሦስት አህጉራትን (ከኤሽያ እስከ ቻይና፣ መላው አፍሪካ እና በአውሮፓ እስከ ስፔይን) ለማዳረስ ችሏል።

## 9. በኢስላም ስም ፈጠራን (ቢድዓን) የማስፋፋት አደጋ

አላህ ሙስሊሞች እርስ በእርሳቸው እንዳይከፋፈሉ አዟል። ሙስሊሞች በኃይማኖት እና በአምልኮ ተግባራት ላይ የሚያካሂዷቸው ፈጠራዎች እና መከፋፈሎች በኢስላም እንደ ብክለት፣ ስህተት እና ማፈንገጥ ይቆጠራል። (ሆኖም በሌሎች የህይወት ዘርፎች ለምሳሌ በሳይንስና ቴክኖሎጂ የሚካሄዱ የሰው ልጅ ህይወትን የሚለውጡ ፈጠራዎች በኢስላም በእጅጉ ይበረታታሉ)።

ቀደም ባሉ ዘመናት የተካሄዱ አንድ ፈጣሪን ከመገዛት እምነት የማፈንገጥ ተግባራት የአላህን ውግዘት እና ውድመት አስከትለው አልፈዋል። እጅግ አዛኝ የሆነው አላህ በነቢዩ ሙሀመድ እድሜ መጨረሻ አካባቢ ባወረደው የቁርዓን አንቀጽ የኢስላም እምነትን እንዳሟላልን ገልጿል። በአምልኮ ተግባራት ላይ የሚካሄድ ማንኛውም ለውጥ በጥብቅ የተከለከለ መሆኑን ሙስሊሞች ልብ ሊሉት ይገባል። በሸይጣን ተጽዕኖ ሥር የሆነው የሰው ልጅ የሚያደርገው ለውጥ አላህ ምሉእና ፍፁም አድርጎ ያወረደውን የእስልምና እምነት ከማቆሸሽ ያለፈ ፋይዳ አይኖረውም። ኢስላም ላይ የሚተገበሩ ፈጠራዎች ሁሉ ቀጥተኛውን መንገድ ያስታሉ። ቀጥተኛውን መንገድ መሳት ደግሞ ለጀሃነም ይዳርጋል። ሙስሊሞች የዚህ ዓይነት ፈጠራ

(መጨመርም ሆነ መቀነስ) የብናኝ ያህል ቢሆን እንኳን ሲፈፀም በቸልታ ማለፍ የለባቸውም::[14] ፈጠራዎች በቸልታ ከታለፉ በሚቀጥሉት ትውልዶች እንደ መደበኛ የዒባዳ ተግባራት ተደርገው በመውሰድ አላህ ምሉእ አድርጎ ካወረደው ኢስላም ውጭ የሆነ ሰው ሠራሽ ኃይማኖት የመፍጠር አደጋ ሊደቅኑ ይችላሉ:: በዒባዳ ተግባራት ላይ ከተገኘበት ሁሉ የመቃረን ወይም የኃይማኖት አባቶችን በጭፍን የመከተል አዝማሚያ በኢስላም ተቀባይነት የለውም::

የአላህ ህጎችን መቀየር በኢስላም የተከለከለ ነው:: አላህ መለኮታዊ መመሪያዎችን የሚለውጡ የኃይማኖት መሪዎችን አውግዟል:: እነዚህ መመሪያዎችን ለመለወጥ የሞከረ ሰው ራሱን ከአላህ ለማስተካከል ጥሯል እና ባእድ አምልኮ ፈፅሟል:: ያለ አግባብ ሰው መግደልን የሚፈቅድ ህግ ማውጣት ለዚህ እንደ አንድ ምሳሌ ሊወሰድ ይችላል:: የአላህ ህጋት ፍፁም ስለሆኑ ምንም ዓይነት ዝመና (Modernization) አያስፈልጋቸውም:: አላህ የእሱን እምነት በመከተል የመታዘዝ አሊያም የራሳችንን ስሜት በመከተል ያለመታዘዝ ሙሉ ነፃነት ሰጥቶናል:: ሆኖም የእርሱ መመሪያዎች ላይ ፈጠራን በመጨመር መቀየርን አልፈቀደልንም::

---

[14] ማንኛውንም ዓይነት የአምልኮ ተግባራትን በአላህ ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኝ ሁለት መስፈርቶች የግድ ማሟላት እንዳለብን ኢስላም ያስተምራል:: እነዚህም:- 1) የአምልኮ ተግባሩን ለመሥራት የተነሳሳው የአላህ ውዴታ ብቻ በመሻት መሆን አለበት:: 2) የአምልኮ ተግባሩን የፈፀምነው ነቢዩ ሙሀመድ (ሰ.ዐ.ወ) ባሳዩን መንገድ መሆን አለበት::

## 10. የአደምና የሐዋ ታሪክ

የአደም እና የሐዋ ታሪክ ቁርዓን ውስጥ ሰፍሮ ይገኛል:: በቁርዓን የሰፈረው ታሪክ በሌሎች እምነት መጽሐፍት ውስጥ ከተገለፀው በብዙ መልኩ ቢመሳሰልም መሠረታዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ልዩነት አለው::

አላህ በመሬት ላይ አዲስ ዘር እንደሚፈጥር ለመላኢካዎች ገልፆላቸዋል:: ከተቦካ ጭቃ አደምን ፈጥሮ ነፍስ ከዘራበት በኋላ የሁሉንም ነገሮች ስም አስተማረው:: ሐዋን ደግሞ ከአደም ፈጠረ:: ሁለቱም በጀነት የፈለጉትን እያደረጉ በነፃነት እንዲኖሩ ፈቀደላቸው::

አላህ አደምን ከጭቃ ፈጥሮ ለመላዕክት "ሱጁድ አድርጉለት /ስገዱለት/" ባለ ጊዜ (አደምን ለማምለክ ሳይሆን ለክብር) ሁሉም ሱጁድ ሲወርዱ ከመካከላቸው ይገኝ የነበረውና ከመላዕክት ሳይሆን ከጅን[15] ወገን የሆነው ሸይጣን በኩራት እና በትዕቢት ሳያደርገው ቀረ:: እሱ ከአደም በፊት ከጭስ አልባ ነበልባል ከተፈጠረው እና የመምረጥ ነፃነት ከነበረው ጅን ዝርያ ውስጥ ነው:: እሱ ከእሳት ተፈጥሮ ከጭቃ ለተፈጠረው አደም "መስገድ"ን እንደ ውርደት መቁጠሩ ነበር:: በእርግጥ ሸይጣን የመጀመሪያው ዘረኛ ነው::

በዚህም ምክንያት ሸይጣን ከአላህ ክብር ወረደ:: ከሁሉም በላይ አዋቂ የሆነው አላህ ሸይጣንን አወገዘው:: ነገር ግን እርጉሙ

---

[15] ጅኖች ከአደም በፊት የተፈጠሩ እና ነፃ ሆነው የመምረጥ አቅም (Free Will) ያላቸው ናቸው:: እምቢተኛ የሆኑ ጅኖች ሸይጣን ይባላሉ:: ከእኛ ጋር እዚሁ ሲኖሩ እራሳቸው መታየትን ፈልገው ካልሆነ በስተቀር ለሰው ልጅ በማይታዩበት ሁኔታ ነው የሚኖሩት:: በኢስላም ክልክል የሆነው ጥንቆላ በጅኖች አማካኝነት ነው የሚሠራው::

ሸይጣን እስከ ፍርዱ ቀን ድረስ ፋታ እንዲሰጠው አላህን ጠይቆ ፈቀደለት:: ፋታውን የፈለገው አደምንና የትውልድ ዘሮቹን ለማሳሳት ነበርና "በእርግጥም ባዶ ተስፋ በመሙላት አሳስታቸዋለሁ" ሲል ፎከረ:: ሸይጣን የሚያውቀውን ሁሉ የሚያውቅ የሆነው አላህ ለሸይጣን የፈቀደለት የሰው ልጅን ለመሞከር ነበር:: እዚህ ጋር ልብ ልንለው የሚገባው ሸይጣን ከፈጠረው ጌታ ጋር ጦርነት የሚገጥምበት ምንም አቅምም ሆነ እድል የሌለው መሆኑን ነው:: ምክንያቱም ልክ እንደሌላው ፍጡር ሁሉ ሸይጣንም የሚኖረው በአላህ ፍላጎት እና ስልጣን ነው:: አላህ ሸይጣንና አጫፋሪዎቹ እንዳይኖሩ ቢፈልግ ኖሮ ለአፍታም መቆየት አይችሉም ነበር::

ኢስላም የአላህን መለኮታዊ ወይም የጌትነት ሥልጣንን ለሸይጣን በምንም መልኩ አይሰጥም:: ሸይጣን ፍጡር ስለሆነ የፈጣሪ ባህሪም ሆነ መለኮታዊነት አይገባውም:: ሸይጣን ለሰው ልጅ ግልፅ ጠላቱ ነው:: ኢስላም ሸይጣንን ከአላህ ጋር ጦርነት ገጥሞ የጀነትን ሲሶ ይወርሳል የሚለውን የአንዳንድ ሰዎች እሳቤ ይቃወማል::

ኩራተኛ፣ እርጉም እና ከአላህ እዝነት የተባረረው ሸይጣን አላህ ለፈጠረው ዓላማ እያገለገለ ነው:: አላህ ለሰው ልጆች ክፉ እና ደጉን በመለየት የመምረጥ ነፃነት አጎናጽፏቸዋል:: ሲፈጥራቸውም እሱን የሚያውቁበት፣ የሚገዙበት ችሎታ አብሮ ፈጥሮላቸዋል:: የሰው ልጅ በተፈጥሮው ጥሩ ነው፤ ሲወለድም ሙስሊም በመሆን በንፅህና ይወለዳል:: ሸይጣንና ግብረ-አበሮቹ ደግሞ የሰው ልጅ ከትክክለኛው የአላህ መንገድ ወጥቶ ጣዖት

አምላኪ እንዲሆን እና ኃጢያት ላይ እንዲወድቅ ከመጣር በዝነው አያውቁም። ሁሉን አዋቂ የሆነው አላህ ሙስሊሞች መልካም እንዲሠሩ እና ከኃጢያት እንዲርቁ ይጋብዛል። የሰው ልጅ ክፉ እና ደጉን የመምረጥ ነፃነቱን ተጠቅሞ ለሸይጣን ተንኮል ባለመንበርከክ ከፍተኛ የሆነ የክብር ደረጃ እና መንበር ሊቆናጠጥ ይችላል።

የአደም እና የሐዋ የጀነት ሙከራ ሲጠቃለል የሚከተለውን ይመስላል። ሁለቱም በጀነት በፍፁም ነፃነት እና ደስታ ይኖሩ ነበር። አላህ ከጀነት ዛፍ ፍሬዎች የፈለጉትን ዓይነት እና የፍላጎታቸውን ያህል እንዲበሉ ፈቀደላቸው። አንድን ዛፍ ግን እንዳይቀርቡት አስጠነቀቃቸው። ማስጠንቀቂያውን ችላ ብለው ከበሉም ከተሳሳቾች እንደሚሆኑ ነገራቸው። ሸይጣን "አላህ እንዳትበሉ የከለከላችሁ ፍሬው ከተበላ ሞት አስቀርቶ እንደ መልዓክ ሊያደርጋችሁ ስለሚችል ነው" በማለት አደምንና ሐዋን አታለላቸው። እናም አደም እና ሐዋ ለሸይጣን መሰሪ ጉትጎታ እጃቸውን ሰጡ፤ ከተከለከሉት ፍሬም በሉ። ከዚያም በኋላ በጥፋታቸው አፈሩ። በልባዊ ፀፀትም ወደ አላህ ተመለሱ። ሁሉን መሀሪ፣ እጅግ በጣም አዛኝ እና እጅግ በጣም ርሁሩህ የሆነው አላህም ይቅር አላቸው። ኢስላም "በአደም ጥፋት ሳቢያ የሰው ልጅ በኃጢያት ይወለዳል" የሚለውን እሳቤ የማይቀበለው በዚህ ምክንያት ነው። ፍትሀዊው አላህ የማንንም ወንጀል ለማንም አይሸከምም። እያንዳንዱ ግለሰብ እራሱ በሠራው ወንጀል እንጂ አይጠየቅም። ሲወለደም ከወንጀል ነፃ ሆኖ በሙስሊምነት ነው። ኢስላም ለአደም እና ሐዋ ስህተት ሐዋን ብቻ ተጠያቂ

እንደማያደርግም ሊጤን ይገባዋል። ምክንያቱም ክፉ እና ደጉን የመምረጥ እኩል ነፃነት ነበራቸው። ከዛፉም የበሉት ሁለቱም ናቸው። እናም የአላህን ትእዛዝ የመጣስ ወንጀል የሠሩት በጋራ ነው። ሌላው ኢስላም በጭራሽ የማይቀበለው አስተሳሰብ "በሐዋ የተነሳ ሴት በአሳሳችነት ስለተረገመች የወር አበባ እና የምጥ ህመም እንዲኖርባት ተደርጋለች" የሚለው ሃሳብ ነው።

አላህ አደም እና ሐዋን በጥፋታቸው ሳቢያ ከጀነቱ አውጥቶ በመሬት ላይ እንዲኖሩ አድርጓል። በመጀመሪያም አዲስ ፍጡር በመሬት ላይ እንደሚፈጠር ለመላዕክት ገልፆ ነበርና። አላህ ጊዜ በማይገድበው እውቀቱ መሬትን የፈጠረው እኛ እንድንኖርበት ነበር።

## 11. ኢየሱስ

ኢየሱስ የአላህ ነቢይ እና መልዕክተኛ ነበር። የተላከውም የአላህን አንድነት እንዲያስተምር ነበር። መለኮታዊነት ይገባኛል ብሎ አልያም እንዲመለክ ጠይቆም አያውቅም። አላህ ለኢየሱስ ከሰጠው ብዙ ተአምራት መካከል ያለ አባት ከድንግል መወለዱ አንዱ ነው። አላህ በቁርዓኑ:- *"አላህ ዘንድ የዒሳ ምሳሌ እንደ አደም ብጤ ነው፤ ከአፈር ፈጠረው፣ ከዚያም ለእርሱ (ሰው) ሁን አለው፤ ሆነም።" /ቁርዓን 3:59/* ብሏል።

አላህ ማንኛውንም ነገር እንደፈጠረ ሁሉ ኢየሱስን ፈጠረ። ሆኖም የኢየሱስ፣ የአደምና የሐዋ አፈጣጠር ለየት ያለ ነው። አላህ ኢየሱስን ያለ አባት፤ አደምና ሐዋን ደግሞ ያለ አባት እና ያለ እናት ፈጥሯል።

ኢየሱስ አላህ የወለደው ልጁ ነው ወይም አላህ እንደ አባት፣ እናት ወይም ልጅ የመሳሰሉት ዘመዶች አሉት ብሎ ማመን የሰው ልጅ ባህሪን ለፈጣሪ ማላበስ ነው::[16] ሙስሊሞች እንዲህ ዓይነት እምነት በጥብቅ የተከለከለ እና ተግባሩም ባዕድ አምልኮ መሆኑን ያምናሉ:: በተመሳሳይም የፈጣሪ መለያ ባህሪያትን ለፍጡር መስጠት ከባድ ኃጢያት ነው:: ለአንድ አምላክ ብቻ ከመገዛት እምነትም ሙሉ በሙሉ ያፈነገጠ ተግባር ነው:: ፍጡርን ወደ ፈጣሪነት ደረጃ ከፍ የማድረግ አመለካከት ከሁሉም የአላህ ነቢያት እና መልዕክተኞች አስተምህሮቶች ጋር የሚፃረር

---

[16] ነቢዩ ዒሳ (ዐ.ሰ) በተወለዱ 325ኛው ዓመት ላይ ኒቂያ (Nicea) በአሁኗ ቱርክ ውስጥ ከእየሩሳሌም ሰሜን እና ሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ በ700 ማይል ወይም በ1100 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ከምሥራቅ ሮማ መዲና አቅራቢያ የምትገኝ ቦታ ላይ አንድ ካውንስል ለመጀመሪያ ጊዜ ተሰብስቦ ነበር:: በዚህ ስብሰባ ላይ ነበር ከተሰብሳቢዎቹ አብላጫ ድምፅ ዒሳ (ዐ.ሰ) በነቢይነት እና መልዕክተኝነት ወደ መለኮታዊ አምላክነት ከፍ የተደረጉት:: የሥላሴ ፅንሰ-ሃሳብ የተገነባው ዒሳ (ዐ.ሰ) ከአላህ ጋር አንድ እና እኩል ናቸው ብሎ በማመን ላይ ነው:: ይህ ፅንሰ-ሃሳብ ኢሳ (ዐ.ሰ) እራሳቸው ሰዎች በጥብቅ እንዲከተሉት ያዙት ከነበረው አንድ ፈጣሪን ብቻ የማምለክ አብራሃማዊ የእምነት መመሪያ ጋር በቀጥታ የሚጋጭ ነው:: ኢስላም የዒሳ (ዐ.ሰ) መፈጠር የተከሰተው፤ አላህ ለሰው ልጆች ምሪት እና እዝነት ብሎ፣ ከማህፀኗ ልጅ እንደሚያስገኝ የሚገልፅ ድንቅ ዜና ለመርየም እንዲያበስሯት ጂብሪልን ባዘዘው ወቅት ነው ብሎ ያስተምራል:: እሷም ያ ድንቅ ዜና ሲደርሳት ናማንም ወንድ ባልቀረበኝ ሁኔታ ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል?ን ብላ ጠየቀች:: ጂብሪልም:- አላህ ሁን ካለው ይሆናልን ሲል መለሰላት:: በዛም ሳቢያ ነው የመርየም ልጅ ዒሳ (ዐ.ሰ) የአላህ ቃል ተብለው የሚጠሩት:: ቃሉ ሁንን የሚለው ነው::

ነው::[17] አላህ ከማንኛውም ፍጡር መለያ ባህሪያት እጅግ የላቀ ነው:: ኢየሱስ እጅግ ርህሩህ በሆነው አላህ የተላከ መሲህ፣ የአላህ ቃል የተቀባ ነቢይና መልዕክተኛ ነው::

አላህ የማርያም ልጅ የሆነው ኢየሱስ እንዳልሞተ እና ወደ እርሱ እንዳሳረገው ይነግረናል:: ሙስሊሞች የኢየሱስ መመለስ እንደ መጨረሻው ቀን መቃረብ ምልክት አድርገው ይወስዱታል:: ኢየሱስ ወደ ምድር በሚመለስበት ጊዜ የነቢይነት እና የመልዕክተኛነት ሚና አይኖረውም:: አዲስ ራእይም ይዞ አይመጣም:: ይልቁንም ከአላህ ለሙሀመድ በወረደው ቁርዓን ይመራል:: የእማኞች መሪ በመሆንም መሬት ላይ ብዙ ፈተናና ጥፋት ይዞ የሚመጣውን ደጃልን ያጠፋል::

## 12. ኃጢያት እና ንሰሀ (ተውባህ)

ኃጢያት የሚባለው በፍላጎት እና ሆን ብሎ የፈጣሪን ትዕዛዝ መጣስ ሲሆን ከኃጢያቶች ሁሉ የከፋው ባዕድ አምልኮ ነው:: ጠባቂው አላህ ለግለሰብ እና ለማህበረሰብ ጎጂ የሆኑ በርካታ ተግባራትን ክልክል አድርጓል:: ነፍስ ማጥፋት፣ ወረራ፣ ሌብነት፣ ማጭበርበር፣ በአራጣ ማበደር፣ ሴተኛ አዳሪነት፣ አስማተኛነት፣ አስካሪ መጠጦችን መውሰድ፣ የአሳማ ስጋ መብላት እና የተከለከሉ መድኃኒቶችን መጠቀም ሁሉ የኃጢያት ተግባራት ናቸው::

---

[17] ክርስቲያኖች እና ይሁዶች የእምነታቸው ምንጭ ከሆነው ከአብረሃም (አንድ አምላክን ብቻ የማምለክ) አስተምህሮቶች ያፈነገጡ ቢሆንም ኢስላም "የመጽሐፉ ባልተቤቶች" እያለ በክብር ይጠራቸዋል:: ኢስላም ክርስቲያኖችን እና ይሁዳዎችን በዚህ ስያሜ የሚጠራቸው ከአላህ በወረዱ አንዳንድ ህግጋት እና ነቢያት በማመናቸው ነው::

በኢስላም ከአባታችን አደም እና ከእናታችን ሐዋ የተወረሰ ኃጢያት አለ የሚለው ሃሳብ ተቀባይነት የለውም:: ማንኛውም ነፍስ የሌላ ነፍስ ኃጢያትን አትሸከምም:: እጅግ ርሁሩህ የሆነው አላህ እራሱ ፍትሀዊ ስለሆነ አንዱ ባጠፋው ሌላውን ተጠያቂ የሚያደርግን ኢ-ፍትሀዊ ተግባር አይፈፅምም::

ማንም ሰው (ወንድም ሆነ ሴት) ኃጢያት በሚሠራበት ጊዜ የአላህ ቅጣት እንደሚጠብቀው ማወቅ አለበት:: እንደ መልካም አጋጣሚ ሆኖ አላህ እጅግ በጣም አዛኝ እና ብዙ ጊዜ መሀሪ በመሆኑ ከልባችን ንስሀ ከገባን ኃጢያታችንን ሊምረን ይችላል:: አላህ የሚያደርጋቸው ነገሮች ሁሉ በገደብ የለሽ እውቀት እና በፍትሀዊነት ነው::

ሙስሊሞች የመርየም ልጅ ኢየሱስ ለሰዎች ልጆች ኃጢያት ሲል ሞቷል ብለው አያምኑም:: እጅግ በጣም ርህሩህ የሆነው አላህ ሊምረው የፈለገውን ሰው ይምራል:: አላህ ኃጢያቶቻችንን ይቅር እንዲለን የኢየሱስ መሰቃየት እና መሞት አስፈላጊ ነበር ብሎ ማመን የአላህን ገደብ የለሽ ሥልጣን፣ ፍትህ እና እዝነት መቃረን ይሆናል::

ለተጠየቀው ሁሉ ምላሽ መስጠት የማይሳነው አላህ ለሠራነው ኃጢያት ከልባችን ተፀፅተን ወደ እሱ በንስሀ ከተመለስን እንደሚምረን ቃል ገብቷል:: ንስሀ አንድ ሰው በአላህ እዝነት ከወንጀል የሚጠራበት መንገድ ነው:: ንስሀ ለሰው ልጅ በጣም አስፈላጊ ጉዳይ ስለሆነ እንደ ቀላል ነገር ሊታይ አይገባም::

እውነተኛ ንስሀ የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርበታል::

1. ንስሀ የሚገባው ሰው ኃጢያት መሥራቱን ተገንዝቦ ከልቡ መፀፀት አለበት::
2. ሰውየው እራሱን ዝቅ በማድረግ ለምህረት ወደ አላህ መመለስ አለበት::
3. ያንን ኃጢያት ላለመድገም ከልቡ መወሰን አለበት::
4. ኃጢያቱ በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ያስከተለ ከሆነ ጉዳቱን ለመካስ የተቻለውን ሁሉ መሞከር አለበት::

ለኃጢያቱ ንስሀ የገባው ሰውዬ ወደፊት ያንን ኃጢያት ደግሞ ቢፈፅመው ቀደም ብሎ የገባው ንስሀ ዋጋ አይኖረውም ማለት አይደለም:: የሚያስፈልገው ዳግመኛ ኃጢያት ላለመሥራት በልቡ ፅኑ ውሳኔ ማድረግ ነው:: ወደፊት ያለው ጊዜ ምን ይዞ እንደሚመጣ ከርሱ በስተቀር የሚያውቅ ስለሌለ አላህ የንስሀ በርን ሁሌ ክፍት አድርጓል:: ሁሌም ይቅር ባይ የሆነው አላህ የአደም ልጆች የርሱን ይቅርታ ፈልገው ወደርሱ ሲመለሱ እጅግ ይደሰታል:: ንስሀ አንዱ የአምልኮ ተግባር ነው::

ከአላህ በስተቀር ኃጢያትን ሊምር የሚችል አካል የለም:: መለኮታዊ ምህረትን ከማንኛውም ፍጡር ወይም በማንኛውም ፍጡር አማላጅነት መፈለግ በጥብቅ የተከለከለ ነው:: ይህ ተግባር በኢስላም እምነት ባዕድ አምልኮ ነው::

## 13. የኢስላም ድርጅታዊ መዋቅር

ኢስላም ግለሰቦች ከአላህ ጋር በሚኖራቸው ግንኙነት ላይ ትልቅ ትኩረት ሰጥቷል:: የግንኙነቱም ሁኔታ ቁርዓን በገለፀውና ነቢዩ ሙሀመድ /ሰ.ዐ.ወ/ ባብራሩት መሠረት ነው የሚሆነው::

ይህም ፍትህ ቅንጅትና ማኅበራዊ መስተጋብር እንዲፈጠር የሚያደርገው ከአላህ ጋር የሚኖረው ግንኙነት በአንፃሩም ሙስሊሞች ከፍጥረታት ሁሉ ጋር ሊኖራቸው የሚገባውን ግንኙነት ይወስናል:: ቁርአን እንዲህ ይላል:-

*"እናንተ ሰዎች ሆይ፤ እኛ ከወንድና ከሴት ፈጠርናችሁ፤ እንድትተዋወቁም ጉሳዎችና ነገዶች አደረግናችሁ:: አላህ ዘንድ በላጫችሁ በጣም አላህን ፈሪያችሁ ነው፤ አላህ ግልፅን አዋቂ ውስጥንም አዋቂ ነው::" /ቁርዓን 49:13/*

የኢስላም መሪ ሊሆኑ የሚገባቸው ብሩህ አዕምሮ ያላቸው አላህን የሚፈሩ የኢስላምን መመሪያዎች በህይወታቸው የሚተረጉሙ ናቸው::

በኢስላም ለቅዱስነት /ለመሪነት/ ተመድቦ የተፈጠረ ሰው የለም:: ማንኛውም በቂ እውቀት ያለው ወይም የተማረና ቁርጠኝነት ያለው ሰው መሪ ሊሆን ይችላል:: ነገር ግን ሁሉም ሰው በቂ ጊዜና አቅም የለውም:: ማንኛውም ሰው አላህ ብቸኛ አምላክና ዕውቀትና መረዳትን የሚሰጥ ጌታ መሆኑን ከግምት ውስጥ አስገብቶ /አውቆ/ እውቀት ለማግኘት የቻለውን ያህል ጥረት ማድረግ ይኖርበታል::

ምሁራን በኢስላማዊ ማኅበረሰብ ውስጥ ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ:: ወንድም ሆነ ሴት ኢስላምን ለማጥናት ለዓመታት ጥረት ያደርጋሉ:: ምሁራን ሰውን ሊባርኩ፣ ኃጢያትን ይቅር ሊሉ ወይም የአላህን ህግጋት ሊቀይሩ አይችሉም:: ነገር ግን ቁርዓንና ሐዲስን በማጣቀስ መረጃዎችን ለሰዎች ያስተላልፋሉ:: በምጡቅ ባህሪያቸውም መልካም ባህሪን እንዲያዳብሩ መንፈሳዊ መነቃቃትን ይጭራሉ:: አንዳንድ ሰዎች ሙስሊም ምሁራንን ለመግለጽ ጳጳስ

/ካህን/ የሚለውን ቃል ይጠቀማሉ:: ይህ የተሳሳተ ስያሜ ነው:: በኢስላም ካህን፣ ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ የሚያስተላልፍም ሆነ የበላይ የሆነ አካል የለም:: በሰዎችና በአላህ መካከል ያለው ግንኙነት ቀጥተኛ ነው:: ከአላህ በስተቀር አንዱን የመፍቀድ አንዱን የመከልከል መብት ያለው የለም:: ማንም ፍጡር ሌላውን ሊባርክ አይችልም:: እያንዳንዱ ሰው ቀጥተኛ ተጠያቂነቱ ለፈጣሪው የተተወ ነው::

አንድ ሰው ወደ መስጊድ ቢገባ በህብረት የሚሰግዱ ሙስሊሞችን የሚመራ ሰው ሊያይ ይችላል:: ሙስሊሞች ተሰብስበው በሚሰግዱበት ማንኛውም ጊዜ ሰላታቸውን በህብረት እና በቅንጅት እንዲሰግዱ አንድ የሚመራቸው ሰው መምረጥ አለባቸው:: ይህም ሰው ካሉት ሰዎች የተሻለ የቁርዓን እና የኢስላም እውቀት ያለው ቢሆን ይመረጣል:: የተመረጠውም ኢማም ይባላል፤ ትርጉሙም መሪ ማለት ነው::

በየሳምንቱ ዓርብ እኩለ-ቀን ላይ በህብረት የሚሰገድ ልዩ ሰላት አለ:: በሰላቱም ሙስሊሞች ሁሉ የመሳተፍ ግዴታ አለባቸው:: በዚህም ቀን ለታዳሚው የሚቀርብ አጭር ንግግር (ኹጥባ) አለ:: ንግግሩን የሚያቀርበው ካሉት ሰዎች ስለ ኢስላም መመሪያዎች የተሻለ እውቀት ያለው ሊሆን ይገባል::

## 14. ኢስላማዊ ሕግ

የኢስላም ህግጋት የሚመነጩት ከቁርዓንና ከነቢዩ ሙሀመድ (ሰ.ዐ.ወ) ንግግር (ሐዲስ) ብቻ ነው:: ልክ እንደ ቁርዓን የነቢዩ ንግግር (ሐዲስ) ከአላህ ነው:: ኢስላማዊው ህግጋት ሁሉንም

የህይወት ዘርፍ ይዳስሳል:: ፍጡራን ከፈጣሪያቸውና ከሌሎች ፍጥረታት ጋር ሊኖራቸው የሚገባቸውን ግንኙነት ይገልፃል:: አላህ ለአማኞች አንዳንድ ሥራዎችን እንዲሠሩ ያዛል:: በሌላ በኩል የተወሰኑ ሥራዎችን እንዳይሠሩ ይከለክላል:: ፍትሀዊና ሁሉን አዋቂ የሆነው አላህ ብቻ ነው አንድን ነገር ክልክል ማድረግ ወይም መፍቀድ የሚችለው::

ሆኖም ኢስላማዊ ማህበረሰብ ከኢስላም ህግ እስካልተጋጨ /የትራፊክ ህግን ይመስል/ ህግ ማውጣት ይችላሉ:: ወደ ቅን መንገድ የሚመራው የዓለማት መሪና አስተዳዳሪ የሆነው አላህ አንዳንድ ተግባራትን ግዴታ ሳያደርጋቸው እንዲሠሩ ይገፋፋል:: ሌሎችን ደግሞ በቀጥታ ክልክል ሳያደርጋቸው እንዲራቁ ይጠቁማል::

እነዚህ ሁሉ ግምት ውስጥ ገብተው የኢስላም ህግ ውስጥ ይካተታሉ:: በነዚህ ላይ ኢስላማዊ ህግ የፈቀዳቸውን ነገሮች ስንጨምር የእያንዳንዱን ሰው እንቅስቃሴ በአምስት መሠረታዊ ክፍሎች ይከፈላል::

1. ግዴታ
2. የሚወደድ
3. የተፈቀደ
4. የተጠላ
5. የተከለከለ

የኢስላም ህግ ምንጩ መለኮታዊ ነው:: እነዚህን የምንተገብራቸው አላህ ስላዘዘን ነው:: ክልክል የሆነበትን ምክንያት ባናውቀውም እንኳን የታዘዝነውን የመፈፀም ግዴታ አለብን:: ነገር ግን ምክንያቱን እንድናጠና እንገፋፋለን፤ ምክንያቱን መረዳት ተጨማሪ ነገር ነው::

ለምሳሌ:- የአሳማ ስጋ መብላት ክልክል ነው:: ምክንያቱ አላህ ክልክል ስላደረገው ነው:: የአሳማ ስጋ ከመብላት የምንቆጠበው የተለየ በሽታ የሚያስተላልፍ እና ለጤንነት ጎጂ መሆኑን በሳይንስ ስለተረጋገጠ ሳይሆን አላህ ክልክል ስላደረገው ነው:: ሳይንቲስቶች የአሳማን ስጋ በሳይንሳዊ ዘዴ ከበሽታ ነፃና በምግብ ተዋፅኦ የዳበረ ቢያደርጉትም የአሳማ ስጋ መብላት ክልክል መሆኑ አይቀርም:: (ግን አንድ ሰው በረሃብ ሊሞት ተቃርቦ በአካባቢው ያገኘው የአሳማ ስጋ ብቻ ከሆነ ህይወቱን ለማትረፍ ሲል ሊበላ ይችላል::) በዚህም ምንም ኃጢያት አይኖርበትም::

የኢስላም ህግ ምንጬ ቁርዓንና የነቢዩ ሱና ነው:: አላህ ክልክል ያደረገው የመፍቀድ ወይም አላህ የፈቀደውን የመከልከል መብት ለኃይማኖት አባቶች መስጠት አላህ በርሱ ላይ እንዳጋሩበት ነው የሚቆጥረው::[18] በዚህ ዓለም አንድን ነገር ጥሩ ነው ወይም መጥፎ ነው ብሎ የመወሰን ሥልጣን የአላህ ብቻ ነው:: በመጭው ዓለም መልካም ሥራ የሠሩትን ምንዳ መስጠትንና መጥፎ የሠሩትን ደግሞ የመቅጣት ሥልጣንና ጥበብ የአላህ ብቻ ነው::

---

[18] በብድር ላይ ማንኛውንም ያህል የወለድ መጠን ማስከፈል ወይም በአራጣ ማበደር በኢስላም ክልክል እንደሆነ ሁሉ በመጀመሪያዎቹ የአይሁድ እና የክርስትና እምነቶች የተከለከለ ነበር:: ይሁን እንጂ በመካከለኛው ዘመን የነበሩት የአውሮፓ ክርስቲያኖች የእምነታቸውን ክልከላ ቀስ በቀስ ቀይረውታል:: በአሁኑ ወቅት "የሙስሊም ሀገሮችም" ጭምር፣ በዚህ በኩል የአላህን ህግ እየጣሱ ይገኛሉ::

## 15. የኢስላም የአለባበስ ሥርዓት

ኢስላም በማህበረሰቡ ውስጥ መልካም ሥነ-ምግባር እንዲስፋፋ ጋጠ-ወጥነት መጥፎ ምግባር እንዲቀንስ ይጥራል:: ይህን እውን ለማድረግ የሰዎች አለባበስ ሥርዓት እንዲኖረው ማድረግን እንደ አንድ መንገድ ይጠቀሙበታል:: ኢስላም ለወንዱም ለሴቱም የግድ ሊሸፍኑት የሚገባ የሰውነት ክፍል እስከ የት መሆን እንዳለበት በግልፅ ያስቀምጣል::

በብዙ ምዕራብ ሀገራትም ሥርዓት ያለው አለባበስን የሚገልጽ ህግ አውጥተዋል:: ይህም የሚያካትተው ለወንድ ሀፍረተ ገላውን ለሴት ደግሞ ከሀፍረተ ገላዋ በተጨማሪ ጡቷን መሸፈን ነው:: አንድ ሰው የአለባበስ ሥርዓት ጥሷል ተብሎ የሚከሰሰውም ይህንን የመጨረሻ ገደብ ሲጥስ ብቻ ነው:: የሴት እና የወንድ አለባበስ ሥርዓት የተለየበት ብቸኛው ምክንያት በተፈጥሮ የሰውነት ቅርፃቸው መለያየት ነው::

ኢስላም ለሴቷም ለወንዱም ጠበቅ ያለ የአለባበስ ህግ አለው:: ወንዶችም ሴቶችም ሥርዓት ያለው ልብስ መልበስ፣ ለኩራት ተብሎ ከሚለበስ እና የሰው ልጅ ክብርን ዝቅ ከሚያደርጉ አለባበሶች እንዲርቁ በኢስላም ታዝዘዋል:: ወንድ ልጅ ሁሌም ቢያንስ ከእምብርቱ እስከ ገልበቱ የሚሸፍን ሰፋ ያለ ልብስ መልበስ ይኖርበታል:: ይሄ ሊቀንሰው የማይችለው የመጨረሻው ገደብ ነው:: ለምሳሌ:- አጭር ቁምጣ ለብሶ አደባባይ መውጣት አይፈቀድለትም:: ሴት ልጅም ከቤት ስትወጣ አካሏን ለህዝብ ከማጋለጥ ታቅባ ቢያንስ ፀጉሯን እና መላ አካላቷን የሚሸፍን ሰፋ ያለ ልብስ መልበስ ይጠበቅባታል:: አንዳንድ ሴቶች ፊታቸውን እና

መዳፋቸውን ጭምር መሸፈንን ይመርጣሉ:: የዚህ ዓይነት አለባበስ አላማው በወንዶችና በሴቶች መካከል አላስፈላጊ የተቃራኒ ፆታ መሳሳብንና የማህበረሰብ ዝቅጠትን በተቻለው ያህል ለመከላከል ነው:: ይህን የአለባበስ ሥርዓት መቀበል ወይም ማክበር የጌታን ትእዛዝ ከማክብር የሚቆጠር ነው::

ኢስላም ከትዳር በፊት ማንኛውንም ስሜት ቀስቃሽ እና ለወሲብ የሚገፋፋ ድርጊት ይቃወማል:: ነገር ግን በተጋቡ ጥንዶች መካከል ስሜት የሚቀሰቅሱ እና ለወሲብ የሚገፋፉ ተግባራት ይበረታታሉ::

አንዳንድ ምዕራባውያን ሴት ልጅ ፀጉሯን እንድትሸፍን የምትደረገው ከወንድ ልጅ የበታች እንደሆነች ለማመልከት ነው ይላሉ:: ይህ ከእውነታው ጋር ምንም ግንኙነት የሌለው እሳቤ ነው:: በኢስላም ሂጃብ የለበሰች (ፀጉሯንና አንገቷን በሚገባ የሸፈነች) ሴት በህብረተሰቡ ዘንድ ክብር ይሰጣታል:: ሥርዓት ባለው አለባበሷም የወንድ ልጅ ስሜት ማራገፊያ ከመሆን ትድናለች:: ኢስላማዊው የአለባበስ ሥርዓት የምትከተል ሴት ለህብረተሰቡ የምታስተላልፈው መልዕክት “በእኔነቴ ልታከብሩኝ ይገባል፤ እኔ የስሜት ማራገፊያ ቁስ አይደለሁም” የሚል ነው:: ኢስላም ያለገደብ ሴትና ወንድ እንዲቀላቀሉ፣ አንዱ የሌላውን ስሜት ለመቀስቀስ እንዲፎካከሩና ልቅ የአለባበስ ሥርዓት እንዲከተሉ መፍቀድ የሚያስከትለው ችግር በግለሰቡ ላይ ብቻ የሚቀር ሳይሆን መላው ማህበረሰቡን የሚያዳርስ መሆኑን ያስተምራል:: ጉዳቱም ከባድ እና ችላ ሊባል የማይቻል ነው::

ሴትን ልጅ ለወንድ ልጅ ደስታ ብሎ የስሜቱ ማራገፊያ እንድትሆን ማድረግ ነፃነት እና እኩልነት አይደለም:: እንዳውም በኢስላም የተከለከለ ኢ-ሰብአዊ ተግባር ነው:: የሙስሊም ሴት ነፃነት የሚገለፀው በውጫዊ ቅርጿ ሳይሆን በባህሪዋ እና በማንነቷ ስትለካ ነው:: ሁሌም ሌላውን ለማስደሰት ለመልካቸው፣ ለቅርፃቸው እና ለወጣትነታቸው እንዲጨነቁ የተገደዱት የምዕራቡ “ነፃ” ሴቶች ከኢስላም እይታ በባርነት ወጥመድ ውስጥ ያሉ ናቸው::

## 16. ሴቶች በኢስላም

አላህ ዘንድ ወንድ እና ሴት እኩል ናቸው:: ሁለቱም ለሠሩት ሥራ በእኩል ይጠየቃሉ:: ለሠሩት መልካም ሥራም በሚቀጥለው ዓለም በእኩል ይመነዳሉ::

ትዳር በኢስላም በጣም የሚበረታታ ህጋዊ ስምምነት እና የተቀደሰ ጥምረት ነው:: ኢስላም ያገባችም ሆነ ያላገባች ሴት የግል መብቷ እንዲከበርላት ያስገነዝባል:: ልክ እንደ ወንዱ የንብረት ባለቤት የመሆን እና ሀብት የማፍራት መብት አላት:: ስትጋባም ሆነ ስትፋታ የግል ንብረቷን ባለቤቷ አይካፈልባትም:: ሴት ልጅ መቼ እና ማንን ማግባት እንዳለባት የመወሰን መብት አላት:: ለባሏ ክብር ሲባል የአባቷን ስም አትቀይርም:: ትዳሯን ካልወደደችውም የፍች ጥያቄ የማቅረብ መብት አላት:: ንግድ ዓለም ውስጥ የመሳተፍ እና ከሌላው የመውረስ መብት አላት:: ሁለቱም በእኩል የመማር፣ የኢስላም ህግጋትን እስካልጣሱ

ድረስም ሁለቱም በእኩል በሥራው ዓለም የመሰማራት መብት አላቸው::

በተለይ መሠረታዊ የኃይማኖቱን ትምህርቶች መማር በወንዱም በሴቷም ላይ ግዴታ ነው:: በተጨማሪም ከሁለቱም ፆታዎች ህዝብን ለማገልገል በተለያዩ የእውቀት ዘርፎች የተካኑ ባለሞያዎች ሊኖሩ ይገባል:: ለምሳሌ:- ዶክተሮች፣ መምህራን፣ አማካሪዎች እና ሌሎችም ባለሙያዎች::

በተለያዩ ማህበራዊ ሥራዎች እና በሌሎችም የሥራ መስኮች ላይ የሚሳተፉ የሠለጠኑ ባለሙያዎች በበቂ ሁኔታ በሌሉበት ማህበረሰብ ውስጥ የሚኖሩ ሙስሊሞች ፍላጎት ለማሟላት ሲባል የባለሙያ እጥረት ባለባቸው የሥራ መስኮች በእውቀቱ መካን ግዴታ ሊሆንባቸው ይችላል::

ሴት ልጅ ኢስላማዊ እውቀት እንድትማር /እንድትፈልግ/ እና ኢስላማዊ ሥርዓቶችን እና ደምቦችን ሳትጥስ ለመማር የምታደርገውን ጥረት ከግብ እንድታደርስ በኢስላም ትበረታታለች:: ለማንም ሰው የመማር መብቷን መግፈፍ ከኢስላም አስተምህሮ ጋር የሚፃረር ተግባር ነው::

ወንድ ልጅ ለቤተሰቡ (ለሚስቱ፣ ለልጆቹ እና ከእርሱ ጋር ለሚኖሩት ሴት ዘመዶቹ) ምግብ፣ ልብስ፣ መጠለያ እና የመሳሰሉትን መሠረታዊ ፍላጎታቸውን በማሟላት የመንከባከብ ግዴታ አለበት:: ሴት ልጅ ባለትዳር ብትሆንም እንኳን በፍላጎቷ ካልሆነ በስተቀር የቤተሰቧን መሠረታዊ ፍላጎቶች የማሟላት ግዴታ የለባትም:: ነቢዩ ሙሀመድ (ሰ.ዐ.ወ) "ከእናንተ መካከል

ይበልጥ አማኝ የሆነው ለሚስቱ የበለጠ መልካም የሆነው ነው" ብለዋል::

## 17. የወንድ ትምክህተኝነት እና ሙስሊሙ ዓለም

ብዙ ሰዎች ኢስላም የወንዶችን ትምክህተኝነት የሚያሰፍንና ሴቶችን በበታችነት የሚያይ እምነት እንደሆነ አድርገው ያስባሉ:: ለዚህ ሃሳባቸውም በአንዳንድ "ሙስሊም ሀገራት" ያሉ ሰዎችን በማስረጃነት ያቀርባሉ::[19] የነዚህ ሰዎች ችግር በማስረጃነት የሚያቀርቧቸው ህዝቦች ባህልና ኢስላማዊ አስተምህሮዎች በመሠረታቸው የተለያዩ መሆናቸውን በወጉ አለመረዳት አልያም ለመረዳት አለመፈለግ ነው:: ድርጊቱም "በሙስሊም ሀገራት" ላይ ብቻ የሚከሰት ወይንም በሁሉም "ሙስሊም ሀገራት" የሚታይ አይደለም::

በዓለም ላይ የሴቶች ጭቆና በብዙ ባህሎች አሁንም በስፋት መቀጠሉ አስደንጋጭ ነው:: በአብዛኛው የሦስተኛው ዓለም ሀገራት ሴቶች በወንዶች ጭቆና ሥር ሆነውና መሠረታዊ የሰው ልጆች መብቶች ተነፍገው የስቃይ ህይወት እየገፉ ይገኛሉ:: ኢስላም ይህንን ጭቆና ይቃወማል፣ ይከላከላል:: ሴትና ወንድ በእኩል ደረጃ መታየት እንዳለባቸው ትኩረት ሰጥቶ በግልፅ ያስተምራል:: በመሆኑም ሰዎች በዘ-ልማድ በሚተገብሯቸው ድርጊቶች ኃይማኖቱን መውቀስ የሚያሳዝን ኢ-ፍትሀዊ ድርጊት ነው:: ድርጊቶቹም ከኢስላም ጋር ምንም የሚያገናኛቸው ነገር እንደሌለ

---

[19] እንደመጥፎ አጋጣሚ ሆኖ አሁን ባለው ሁኔታ "ኢስላማዊ ሀገር" የሚለው መጠሪያ የሚሰጠው ሀገር መንግስቱም ሆነ ህዝቡ በኢስላማዊ ህግ /ሸሪዓ/ ስለሚተዳደር ሳይሆን የሙስሊሞች ሀገር ስለሆነ ብቻ ነው::

በቅጡ ሊጤን ይገባል:: ከነዚህ ድርጊቶች መካከል በአባይ ሸለቆና በአካባቢው በነበሩ እምነት በሌላቸው የጥንት ጕሣዎች የተጀመረው እና አንዳንድ ሰዎች ግርዛት ብለው የሚጠሩት የሴት ልጅ ብልትን የመተልተል ተግባር አንዱ ነው::

በተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት በተለያዩ ጕሳዎች ውስጥ በሚገኙ የተለያየ እምነት ተከታይ በሆኑ ሰዎች ዘንድ እየተተገበረ ያለ ፀያፍ ድርጊት ነው:: በአፍሪካ በተለይም /በሰሜን ምሥራቅ/ የሚገኙ ብዙ ሴቶች የዚህ አረመኔያዊ፣ ዘግናኝና ቅስም ሰባሪ የሆነው ባህላዊ ድርጊት ሰለባ ሆነዋል::

ሴት ልጅን መግረዝ በኢስላም የተጠላና የተከለከለ ተግባር ነው:: ይሁን እንጂ አንዳንድ ነገዶችና ጕሣዎች እስልምናን ከተቀበሉ በኋላ ይህንን ፀያፍ ተግባር ቀጥለውበት ይገኛሉ:: ይህ ተግባራቸው ነው አንዳንድ ሰዎች ሴት ልጅን መግረዝ የኢስላም ኃይማኖት የሚደግፈው እንዲመስላቸው ያደረገው:: በአሁኑ ጊዜ የማህበረሰቦቹ ኢስላማዊ እውቀት ቀስ በቀስ እየዳበረ በመምጣቱ ይህንን ፀያፍ ባህላዊ ተግባር እየተዉት ይገኛሉ:: ለምሳሌ:- በኬንያ ሴት ልጅን ከማይገርዙት የህብረተሰቡ ክፍሎች ዋነኞቹ ሙስሊሞች ናቸው:: የወንድ ልጅ ግርዘት ግን ሙሉ በሙሉ ኢስላማዊ የሆነና ነቢዩላህ ኢብራሂምን ጨምሮ በአላህ መልዕክተኞች ነቢያት እንዲተገበር ትዕዛዝ የተላለፈበት ተግባር ነው:: ሴቶችን መግረዝ ተከልክሎ ወንዶች እንዲገረዙ የታዘዘበት ምክንያት ምንም የሚያደናግር ስላልሆነ ማብራርያ አያስፈልገውም:: ሌላው ያለ አግባብ ኢስላም ላይ የተለጠፈው አሰቃቂና ባህላዊ ድርጊት ቤተሰብን የሚያዋርድ ተግባር ፈፅማለች

በሚል ተልካሻ ምክንያት ሴት ልጅን መግደል ነው:: ሆኖም ድርጊቱ አንዳንዴ የሚከሰት ከመሆኑም በተጨማሪ በህንድ፣ በመካከለኛው ምሥራቅ እና በሌሎች አካባቢ በሚገኙ ውስን የህብረተሰብ ክፍሎች ብቻ የሚተገበር ነው:: ይህ ድርጊት በኢስላም ግልፅ የግድያ ወንጀል ነው:: አንድ ሰው ለክብሩ ብሎ ማንንም እንዲገድል አይፈቀድለትም:: ተግባሩም የኢስላም ህግን የሚፃረር በመሆኑ በምንም መልኩ የኢስላምና የሙስሊሙ ህብረተሰብ መገለጫ ተደርጐ ሊቀርብ አይችልም::

ዘረኝነት፣ ፆታዊ አድሎ ማንኛውም ዓይነት ጠባብነት እና አክራሪነት ወይም ጥላቻ በኢስላም የተከለከለ ነው:: የሚያሳዝነው በብዙ ባህላዊ ህብረተሰቦች ውስጥ ሴትን ልጅ ያለፍቃዷ አስገድዶ መዳር እስካሁንም ሊገታ ያልቻለ ተግባር መሆኑ ነው:: ይህም በኢስላም የተከለከለ ሌላው ተግባር ነው:: በነቢዩ /ሰ.ዐ.ወ/ ዘመን አንድ ወላጅ ልጁን ያለፍቃዷ ዳሯት:: ልጅቷም ወደ ነቢዩ /ሰ.ዐ.ወ/ መጥታ ያለፍቃዷ ተዳርኩ ብላ ክስ ስታቀርብ ምንም እንኳን ኒካሁ የተፈፀመ ቢሆንም ከፈለገች መቀጠል ካልፈለገች ግን ትዳሩን የማፍረስ መብት እንዳላት በመግለፅ ሴቶች ላይ የሚደርሰውን ጭቆና የሚገታና የትዳር አጋርን የመምረጥ ነፃነት እንዳላቸው የሚያስረዳ ለኢስላማዊ ህግ መመሪያ የሆነ መሠረት አስቀመጡ::

የሚያሳዝነው በአጠቃላይ በሁሉም ሀገራት ኢስላማዊ ሀገራትንም ጨምሮ በብዙ የዓለማችን ክፍሎች በዚህ ወቅትም መተግበሩ ነው:: ምንም እንኳን በአጠቃላይ በሁሉም ሀገራት ድርጊቱ ህገ-ወጥ ቢሆንም በባህላዊ ማህበረሰብ ውስጥ የሚኖሩ

ብዙ ሴቶች መብታቸውን አያውቁም ወይም መብታቸውን ለመጠየቅ ድፍረቱ የላቸውም።

## 18. ኢስላም፣ ጦርነትና ጂሀድ

ጥቃት የደረሰባቸው ሰዎች ጠላታቸውን መዋጋት እንደሚችሉ ቁርዓን በግልፅ አስቀምጦታል። አላህ እንዲህ ይላል:- *"እነዚያንም የሚጋደሉዋችሁን /ከሀዲዎች/ በአላህ መንገድ ተጋደሉ፣ ወሰንንም አትለፉ፣ አላህ ወሰን አላፊዎችን አይወድምና።"/ቁርዓን 2:190/*

አላህ በሌላ አንቀፅም እንዲህ ይላል:- *"በአላህ መንገድና ከወንዶች፣ ከሴቶችና ከልጆችም የሆኑትን ደካሞች እነዚያን ጌታችን ሆይ ከዚህች ባለቤቶቿ በዳይ ከሆኑት ከተማ አውጣን፤ ከአንተም ዘንድ ለእኛ አሳዳሪን አድርግልን፤ ከአንተ ዘንድም ለእኛ ረዳትን አድርግልን የሚሉትን /ለማዳን/ የማትጋደሉት ለእናንተ ምን አላችሁ።" /ቁርዓን 4:75/*

በተጨማሪ የቁርዓን ሌላኛው ክፍል ጦርነቱን ማቆምና ስምምነት ማድረግ እየፈለገ መዋጋት ክልክል መሆኑንም ይገልፃል። አላህ እንዲህ ይላል:- *"ቢከለከሉም አላህ መሀሪ፣ አዛኝ ነው። እውከት እስከማይገኝና ኃይማኖት ለአላህ ብቻ እስከሚሆን ድረስ ተጋደሉዋቸው፤ ቢከለከሉም ወሰንን ማለፍ በበዳዮች ላይ እንጂ የለም /ወሰን አትለፉባቸው/።" /ቁርዓን 2:192-193/*

ጭቆናና በደልን ለማስወገድ መዋጋት ይፈቀዳል። ምክንያቱም ማንኛውም ሰው ጌታውን የማምለክ መብት አለውና። ይህ ደግሞ ለኢስላምና ለሙስሊሞች ብቻ ተግባራዊ የሚደረግ አይደለም። አላህ እንዲህ ይላል:-

> *ለነዚያ ለሚገደሉት /ምእመናን/ እነርሱ የተበደሉ በመሆናቸው /መጋደል/ ተፈቀደላቸው፤ አላህም እነርሱን በመርዳት ላይ በእርግጥ ቻይ ነው። ለነዚያ ጌታችን አላህ ነው ከማለታቸው*

*በስተቀር ያለ አግባብ ከሀገራቸው የተባረሩ ለሆኑት /ተፈቀደ/፤ አላህ ሰዎችን ከፊላቸውን በከፊሉ መገፍተሩ ባልነበረ ኖሮ ገዳማት፣ ቤተ ክርስቲያኖችም፣ ምኩራቦችም በውስጣቸው የአላህ ስም በብዛት የሚወሳባቸው መስጊዶችም በተፈረሱ ነበር፤ አላህም ኃይማኖቱን የሚረዳውን ሰው በእርግጥ ይረዳዋል፣ አላህ ብርቱ አሸናፊ ነውና::" /ቁርዓን 22:39-40/*

ይህም ማለት በቁርዓኑ በግልፅ እንደተቀመጠው ሙስሊሞች ኃይሉ ባላቸው ጊዜ በሌላ ቦታ ላይ እምነታቸውን በነፃነት እንዳያካሂዱ ግፍና በደል የሚደርስባቸው የሌላ እምነት ተከታዮች ካሉ ሙስሊሞች ተዋግተው ከግፍና ጭቆና ነፃ የማውጣት ግዴታ አለባቸው::

የሰዎች ሁሉ ህይወት /ሙስሊምም ሆነ ሌላ እምነት ተከታይ/ ክብርና ንብረት በማንም ሊደፈሩ የማይገቡ ቅዱስ ናቸው:: ሁሉም ሰው ጌታውን የማምለክ እና የመረጠውን ጐዳና የመከተል ነፃነት ሊኖረው ይገባል::

የእምነት ጠባቂ የሆነው አላህ እንዲህ ብሎ በግልጽ አስቀምጦታል:: *"በኃይማኖት ማስገደድ የለም::" /ቁርዓን 2:256/*

ይህም ወደ ጂሀድ እሳቤ ይወስደናል:: ጂሀድ የሚለው ቃል ጥሬ ትርጉሙ መታገል ወይም ጥረት ማድረግ ማለት ሲሆን ማንኛውንም ተግባር ለመፈፀም የሚደረግ ከፍተኛ ጥረትን ያካትታል:: ጂሀድ በቀጥታ ጦርነትን የሚያመለክት ቃል አይደለም:: ከግላዊ ስሜት ወይም ከመጥፎ ዝንባሌ ራስን ማቀብም ጂሀድ ሊሆን ይችላል:: እንዲሁም ምድር ላይ ፍትህ፣ ሠላምና እኩልነት እንዲሰፍን መጣርም ጂሀድ ይባላል::

በኢስላምም ሆነ በቁርዓን "ቅዱስ ጦርነት " የሚባል ነገር የለም:: ይህ የተዛባ የጂሀድ ትርጓሜ ነው:: አንዳንድ ሰዎች ሙስሊሞች የሌላ እምነት ተከታዮችን አስገድደው ሙስሊም የሚያደርጉበትን ተግባር ቅዱስ ጦርነት ብለው ይጠሩታል ይላሉ:: ሆኖም በኢስላም የሌላ እምነት ተከታዮችን አስገድዶ ሙስሊም ማድረግ ፈፅሞ የተከለከለ ተግባር ነው::

በኢስላም ውጊያ ላይ መሳተፍ ጂሀድ የሚሆንበት ወቅት አለ:: ነገር ግን ምን ምን ሲያሟላ ነው ውጊያ እንደ ጂሀድ የሚቆጠረው የሚለው ወሳኝ ጥያቄ ነው:: ጦርነት የጂሀድ ማዕረግ የሚጐናፀፈው ለአላህ ተብሎና አላህ ባስቀመጠው ህግና ደንብ መሠረት ሲሆን ነው:: ሀብት ለማጋበስ፣ ለሀገር፣ ለወገን፣ ለዘር፣ ለክብር፣ ለድንበር ብሎ መዋጋት በፍፁም ከጂሀድ ሊቆጠር አይችልም:: በጂሀድ ጦርነት በሌሎች ጦርነቶች ላይ የማይታዩ ራስን የመቆጣጠር ጥብቅ ደንቦች አሉት:: ሰዎች ስለወረሯቸው ለመበቀል መዋጋት እንኳን ከጂሀድ አይቆጠርም::

ከነቢዩ ሙሀመድ የህይወት ታሪክ ጂሀድ እንዴት መካሄድ እንዳለበት የሚያሳየንን ጥሩ ተሞክሮ እናገኛለን:: ነቢዩ ሙሀመድ የመካ ህዝቦችን በሠላማዊ መንገድ ወደ ኢስላም ሲጣሩ ጠንካራ ተቃውሞ ገጥሟቸው ነበር:: ሙስሊም በመሆናቸው ምክንያት ብቻ ነቢዩ እና ተከታዮቻቸው ከባድ ስቃይ ደርሶባቸዋል:: ማዕቀብ ተጥሎባቸዋል፣ ከሀገር ተባረዋል፣ ተገርፈዋል፣ ተደብድበዋል፣ ታስረዋል፣ ንብረታቸውም ተዘርፏል:: አልፎ ተርፎም ተገድለዋል::

ሙስሊሞች ይህ ሁሉ መከራ እና ስቃይ እየደረሰባቸው ሠላማዊ መንገድ እንዲከተሉ እና አደጋ እንዳይደርስባቸው ራሳቸውን እንዲጠብቁ ከሚያዝዘው ኢስላማዊ መመሪያ አላፈነገጡም:: ነቢዩ ሙሀመድ ለ10 ዓመታት መካ ውስጥ ኢስላምን ካስተማሩ በኋላ በርካታ የመካ "ታላላቅ" ሹማምንት እና መሪዎች ነቢዩን በድብቅ ለመግደል በማሴር ከተለያዩ ጎሳዎች ጋር በማበር ከሁሉም የተውጣጣ ጥምር ኃይል አቋቋሙ:: አላህ በመልዓኩ ጂብሪል አማካኝነት ሁኔታውን ለነቢዩ በማሳወቅ ሴራቸውን አጋለጠ::

ሊገድሏቸው ባሰቡበት ሌሊትም ነቢዩ ሙሀመድ (ሰ.ዐ.ወ) ከመካ ወደ መዲና ተሰደዱ::[20] ሴረኞቹም ነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ) ለመያዝ ለቀናት ክትትል አድርገውባቸዋል:: ሁኔታውም እየተባባሰ ሄዶ ሙስሊሞች ሁሉ እንዲሰደዱ ግድ የሚሆንበት ደረጃ ላይ ደረሰ:: ነቢዩ ሙሀመድን (ሰ.ዐ.ወ) እንደ መሪ እና ነቢይ በፍቅርና በጋለ ስሜት የተቀበሉት በስተሰሜን በምትገኘው መዲና ውስጥ የሚኖሩ ህዝቦች ተሰደው ወደነርሱ እንዲመጡ ግልፅ ጥሪ አደረጉላቸው:: በመዲናም ኢስላማዊ ማህበረሰብ ተገንብቶ ነቢዩ ሙሀመድ (ሰ.ዐ.ወ) ወደ ኢስላም ጥሪ የማድረግ ሠላማዊ ተልዕኳቸውን ቀጠሉ::

የመካ ጥምር ኃይል ኢስላም ነቢዩ ሙሀመድንና አሃዳዊ አስተምህሮቱን ለአንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ ለማጥፋት ቆርጠው

---

[20] ነቢዩ ሙሀመድ (ሰ.ዐ.ወ) ከመካ ወደ መዲና ያደረጉት ስደት ሂጅራ በመባል ይታወቃል:: ኢስላማዊ የቀን አቆጣጠር (ካሌንደር) የሚጀምረውም ከዚህ ስደት ነው:: ካሌንደሩ አሥራ ሁለት ወሮች ሲኖሩት እያንዳንዱ ወር የሚጀምረው አዲስ ጨረቃ ከወጣችበት ዕለት ነው:: ይህ አቆጣጠር 12 የጨረቃ ወራት ከነበሩት ጥንታዊው የሂብሩ ካሌንደር ጋር ተመሳሳይ ነው::

ነበር:: ከሙስሊሙ በቁጥር እጅግ የሚበልጠው እና በሚገባ የታጠቀው ወራሪ ኃይል ከየአቅጣጫው ብቅ ሲል ጥበበኛው አላህ ለሙስሊሞች ለመጀመሪያ ጊዜ እራሳቸውንና ኃይማኖታቸውን (እምነታቸውን) ለመከላከል እጃቸውን እንዲያነሱ ፈቀደላቸው:: ጣዖት አምላኪው የመካ ጦር በቁጥር እና በትጥቅ ከሙስሊሙ ጦር እጅግ ብልጫ የነበረው ቢሆንም የእምነት ፅናት በነበራቸው ጥቂት ሙስሊሞች ተሸነፈ:: የመካው ጥምር ጦር ጦርነት እንደማያዋጣው ከተገነዘበ በኋላ በነቢዩ ሙሀመድ እና በመካ መሪዎች መካከል ለተደረገው የሠላም ስምምነት ግፊት አደረገ:: ሙስሊሞች በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ሠላምን ለማስፈን እንዲታገሉ አላህ አዟል:: ስለዚህ ስምምነቱ ተደረገ:: ይህ ስምምነት ያልታጠቁ ሙስሊሞች የሐጅ ሥርዓት ለመፈፀም በኢብራሂም ወደተገነባው ካዕባ እንዲሄዱ አስችሏል:: ስምምነቱ በተፈጠረው መልካም አጋጣሚ ብዙ ሰዎች ወደ ኢስላም ሲገቡ የመካ መሪዎች ባዩ ጊዜ የሠላም ስምምነቱ ለእነሱ ጉዳት እንደሆነ ተረዱ:: እናም ሠላም እና ኢስላምን ለማጥፋት ሌላ የክህደት ሴራ በመጠንሰስ ሙስሊሞችን የማጥቃት እና የመግደል እርምጃ ወሰዱ:: የመካ መሪዎች የቃል-ኪዳን ውሉን ካፈረሱ በኋላ ነበር ሙስሊሞች ይህንን አምባገነናዊ ድርጊት ለማስቆም እንዲዋጉ አላህ በቁርዓኑ ያዘዛቸው:: በሚገርም ሁኔታም ሙስሊሞች ያለምንም ደም መፋሰስ መካን በቁጥጥራቸው ሥር አደረጉ::

ለመካ ሰዎች በሙሉ ይቅር ብለው ከጥቃት ነፃ መሆናቸውን አበሰሯቸው:: በዙሪያዋ ከተሰቀሉት ጣዖታት አምልኮ አፀዷት:: ነቢዩ ሙሀመድም (ሰ.ዐ.ወ) በመካ ሰዎች ላይ ምንም

ዓይነት ጭቆና፣ በደል፣ ኃይማኖታቸውን አስገድዶ የማስቀየር እና የተዘጉ በሮቻቸውን በኃይል ከፍቶ የመግባት ተግባር ክልክል አደረጉ:: እንዲሁም ደግሞ ሲገድሏቸው ጥረት ያደርጉ የነበሩ እና ብዙ ስቃይ ያደረሱባቸው ከዚህም አልፎ የቤተሰባቸውን አባላት የገደሉባቸው ቀንደኛ ጠላቶቻቸውን ሳይቀር በርህራሄ ይቅር አሉ:: ትክክለኛው ጂሀድ ይህ ነው:: ትክክለኛ የኢስላም ምሳሌ የሰብዓዊነት ቁንጮ እና የጂሀድ አርአያ የነበሩት ነቢዩ ሙሀመድም እኚህ ናቸው::

የሚቀጥለው ታሪክ በኢስላም ጦርነት እንዴት ይካሄድ እንደነበር ይበልጥ ግልፅ ያደርግልናል:: ነቢዩ ሙሀመድ ጦርነት ላይ ያልተሳተፈ ሠላማዊ ሰውን መግደል ከልክለዋል:: የነቢዩ ባልደረባ የነበሩት ዑመር እንዲህ ይላሉ:- "ነቢዩ እያሉ በተደረገ አንድ ጦርነት አንዲት የተገደለች ሴት አየሁኝ:: ነቢዩም ሴትና ህፃናትን መግደል ከለከሉ::" ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል::

ሌላው የነቢዩ ባልደረባ የነበረው ረቢዕ ቢን ረቢዕ በአንድ ጦርነት ያጋጠመውን ሁኔታ እንደሚከተለው ገልጿል:: "እኛ በአንድ ጦርነት ከአላህ መልዕክተኛ ጋር ሆነን የተሰበሰቡ ሰዎችን አየን:: ነቢዩም ሰዎች ለምን እንደተሰበሰቡ የሚያጣራ ሰው በፍጥነት ላኩ:: የተላከውም ሰውዬ ሰዎች የተሰበሰቡት በአንድ የተገደለች ሴት ዙሪያ መሆኑን ነገራቸው:: መልዕክተኛውም ልትጠቃ (ልትገደል) አይገባም ነበር አሉ:: ጦርነቱን የሚመራው ኻሊድ ቢን ወሊድ ነበርና ሴቶችንና ሠላማዊ ሰዎችን እንዳትገድሉ ብለው ለኻሊድ ቢን ወሊድ መልዕክት ላኩበት::" አቡ ዳውድ ዘግበውታል::

የአላህ መልዕክተኛ ጦር ሲልኩም "በአላህ ስም ወደፊት ገስግሱ:: ሽማግሌዎችንና ህፃናትን አትግደሉ፣ ድንበርንም አትለፉ" ይሉ ነበር:: ሙወጣዕ ዘግበውታል::

ከነዚህ የኢስላም አስተምህሮዎችና ሐዲሶች ኢስላም ሽብርተኝነት ላይ ያለውን አቋም በቀላሉ መረዳት እንችላለን:: አሸባሪነት ከኢስላም መመሪያ ጋር የሚጋጭ ነው:: አሸባሪነት ህብረተሰብን ስጋት ውስጥ ለመክተት ሠላማዊ ሰዎች ላይ ያነጣጠረ ጦርነት ነው:: ከላይ ከተጠቀሱት ሐዲሶች የምንረዳው በጦርነት ላይ ቢሆን እንኳን የታጠቁ ቀንደኛ ተዋጊዎችን እንጂ ሠላማዊ ሰዎችን መግደል፣ ንብረትም ሆነ አትክልት ማውደም ለሙስሊም ተዋጊዎች አይፈቀደም:: ይህ በኢስላም ህግና በግልፅ በተቀመጠው በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሱና በጥብቅ የተከለከለ ነው:: ሠላማዊ ሰው መግደል በጦርነት ላይ ሆኖ የጠላት ኃይል ሠላማዊ ሰዎችን በመግደል ድንበር ቢተላለፍ እንኳን የአላህን ሕግም ሰብዓዊነትንም የሚቃረን የነፍስ ማጥፋት ወንጀል ነው:: ሆን ብሎ አንድ ሠላማዊ ሰውን የገደለ ላጠፋው ነፍስ ቅጣት የሚገባው ነፍሰ ገዳይ ነው:: አሸባሪነት በግልፅ ቋንቋ በኢሰላም ክልክል የተደረገ ተግባር ነው:: ኢስላማዊ ህግ የኀሪላ ውጊያ ውጤት ያስገኛል የሚለውን ሀሳብ ይቃወማል::

በኢስላም ታሪክ የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሱናን በትክክል ይተገብሩ የነበሩት የመጀመሪያው ትውልድ "ሶሐባ" ባህሪና ከጠላት ጋር የነበራቸው ግንኙነት ምን ይመስል እንደነበር ብናይ አሁን በምን መልኩ ማካሄድ እንዳለብን ጥሩ ሞዴል እናገኛለን::

የነቢዩ ሙሀመድ (ሰ.ዐ.ወ) ባልደረባ፣ ምትክና መሪ የነበሩት የመጀመሪያው ኸሊፋ አቡበክር (ረ.ዐ.) አምባገነን ወደነበረው የሮማ አስተዳዳሪ ወደ ሶሪያ ጦር ሲልኩ የማበረታቻ ቃል ሊሰጧቸውና ሊሸኟቸው ወጥተው "የምትሄዱበት ሀገር ጌታን የሚገዙ ህዝቦች (ቀሳውስት) ታገኛላችሁ:: ባሉበት እምነት ተውዋቸው:: ኃይማኖታቸውን ለመፈፀም ነፃነት እንዳትነፍጓቸው" ብለው መከሯቸው::

በሁለተኛው መሪ (ኸሊፋ) ጊዜም እየሩሳሌምን ሙስሊሞች ከሮማ አምባገነን ገዢ ነፃ ሲያደርጓት ህዝቡ ነፃ ሊያወጡት መምጣታቸውን አምኖ ተቀብሎ ነበር:: ምንም እንኳን ሙስሊሞች ሀገሩን ቢቆጣጠሩትም ህዝቡን እንደጠላት እንዲያዩት ግን አልተፈቀደላቸውም:: የነርሱ ጠላት ህዝቡን ሲጨቁን የነበረው የሮማ አምባገነን መሪ ብቻ ነበር:: ዑመር (ረ.ዐ.) እየሩሳሌምን ተቆጣጥረው በትህትናና በሥርዓት ገብተው ከመሠረቱ ክርስቲያን ለነበሩ ህዝቦች ማስፈራራትና ወቀሳ ሳይሆን በእየሩሳሌም ክልል ውስጥ ምንም አደጋ እንደማይደርስባቸው በመግለፅ የሚያረጋጋ አዋጅ ነበር ያወጁት:: ከዚህ ቀጥሎ ያለው ከረቂቅ ስምምነቱ የተወሰደ ነው::

> *ይህ የእማኞች መሪ የሆነው ዑመር ለህዝቡ ያስተላለፈው የጦርነት ማቆም ስምምነት ማረጋገጫ ነው:: በሠላም እንደምትኖሩ ቃል እገባላችኋለሁ:: በራሳችሁ ላይ፣ በቤተክርስቲያናችሁና በመስቀላችሁ ላይም ምንም ዓይነት አደጋ እንደማይደርስባችሁ ቃል ይገባላችኋል:: ቤተክርስቲያኖቻችሁ አይዘጉም፣ አይፈርሱም፣ በውስጣቸው ያሉ ንብረቶችም አይዘረፉባችሁም፣ መስቀሎቻችሁም*

*አይነኩባችሁም፣ ኃይማኖታችሁን እንድትቀይሩም አትገደዱም:: ምንም ዓይነት መንሳቆልም አይደርስባችሁም::*

በድጋሚ ለመግለፅ በኢስላም ቅዱስ ጦርነት የለም:: ጦርነት መጥፎ የሆነ የጭካኔ ተግባር ነው:: በፍፁም ቅዱስ ሊሆን አይችልም:: ሙስሊም በምንም መልኩ የሌላ እምነት ተከታይ ላይ ጫና እንዲያደርግ አይፈቀድለትም::

ጂሀድ ማለት ትግል ማለት ነው:: ይህ ትግል ወታደራዊ ይዘት ሊኖረው ይችላል:: ይሄኔ በጂሀድና በጦርነት መካከል ያለው ልዩነት ግልፅ ይሆናል:: ጂሀድ ለዓለማዊ ጥቅም፣ አንድ ሀገርን ለመውረር ወይም ለመበቀል ተብሎ በፍፁም ሊካሄድ አይችልም:: የማንኛውም እምነት ተከታይ "ጌታውን" የማምለክ ነፃነቱ በኃይልና በጉልበት ሲገፈፍ ሙስሊሞች ነፃነቱን የማስከበር ግዴታ አለባቸው:: ነገር ግን በራሳቸው ላይ ጥቃት ቢደርስ እንኳን ሠላማዊ ሰውን ማጥቃት በፍፁም አይፈቀድላቸውም::

## 19. ሳይንስና ቴክኖሎጂ

ኢስላምን ልዩ ከሚያደርገው ባህሪ አንዱ ከትክክለኛ ሳይንስ ጋር ሙሉ ለሙሉ የሚስማማ መሆኑ ነው:: ሙስሊሞች ሳይንሳዊ እውነታና ኃይማኖታዊ አስተምህሮቶች ሊጋጩ አይችሉም ብለው ያምናሉ::

ኃይማኖት የመጣው መጀመሪያና መጨረሻ ከሌለው ዓለምን ለብቻው ካስገኘ አምላክ ነው:: ስለዚህ አንዱ (ኃይማኖት) ከአንዱ (ከሳይንስ) ሊጋጭ አይችልም::

ሙስሊሞች አላህ ለፈጠረው ነገር ሁሉ ተፈጥሯዊ (ሳይንሳዊ) ትንተና ሊገኝለት ይችላል ብለው ያምናሉ::

ሙስሊሞች ተፈጥሯዊ ጉዳዮችን ለማብራራት በተዓምር ላይ አይንጠለጠሉም:: አንድ ሙስሊም ተአምራት ማለት አላህ እራሱ ካስቀመጣቸው ተፈጥሮአዊ ህጎች ውጪ በሆነ ሁኔታ ነቢያትን ለማገዝ፣ ለተለመነው ነገር መልስ ለመስጠት ሲል ወይም በሌላ ምክንያት የሚፈፅማቸው ነገሮች እንደሆኑ ያምናል:: በተጨባጩ ዓለም የሚከሰቱ ነገሮችን ለማብራራት ወይም የሰውን ልጅ አንድ ሳይንሳዊ ጉዳይ ላይ ያለበትን አላዋቂነት ለመሸፋፈን ሲባል ተዓምራዊ ማብራሪያዎች መቅረብ የለባቸውም::

ከኢስላማዊ አስተምህሮ ጋር የሚጋጭ አንድም ሳይንሳዊ እውነታም ሆነ ትክክለኛ የሆነ ሳይንሳዊ ንድፈ-ሀሳብ የለም:: ማንኛ ውም ሳይንስ የሚደርስባቸው ግኝቶች የአላህን ፍጥረታት እፁብ ድንቅነታቸውን ይበልጥ እንድንረዳ ነው የሚያደርጉን:: ለዚህ ነው ኢስላም ሳይንሳዊ ግኝቶችንና ፈጠራዎች ላይ ጥናት እንድናደርግ የሚገፋፋንና ቁርዓንም በዓለም ላይ የሚገኙ የአላህ ተዓምራትን (ፍጥረታትን) እንድናጠናና እንድናስተነትን የሚያዘን:: በእርግጥ ቁርዓን በዚህ ዘመን ለሚገኘው ሳይንስ እድገት የሚጠቅሙና በቅርቡ ሙሉ በሙሉ የታወቁ አስደናቂ ሳይንሳዊ መረጃዎችን ይዟል:: ኢስላም የሰው ልጅ ምጥቀት ውጤቶችን እንድንጠቀምባቸው ፈቅዷል:: ዓለምን ለማሻሻል ትግል እንድናደርግም ግፊት ያደርጋል:: ኢስላም የቴክኖሎጂ ውጤቶችን በፀጋ ይቀበላል:: ቴክኖሎጂን ለጥሩም ለመጥፎም ልንገለገልበት እንችላለን:: ቴክኖሎጂ በራሱ ጎጂም ጠቃሚም አይደለም:: ፈጣሪ የሰጠንን ዕውቀት የሰው ልጅን ሁሉ ህይወት ሊያሻሽል ለሚችል ነገር ማዋል የኛ ኃላፊነት ነው::

ሰዎች የኢስላምን ህግና መመሪያ በህይወታቸው በተረጎሙበት የመጀመሪያው ትውልድ ሳይንስ፣ ባህል፣ ንግድና ቴክኖሎጂ አብበው ነበር:: በኢስላሙ ዓለም የነበሩ ምሁራን በሂሳብ፣ በኬሚስትሪ፣ በፊዚክስ፣ በህክምና፣ በሳይንስ፣ በፈለክ ጥናት፣ በህንፃ ጥበብ፣ በሥነ-ጽሁፍ፣ በከርሰ-ምደር፣ በታሪክ እና በሌላም መስኮች ላይ ምርምር አድርገው ለመስኩ ዕድገት ከፍተኛ አስተዋፅዖ አበርክተዋል:: ጥቂቶቹን ለመጥቀስ መግነጢሳዊ ኮምፓስ፣ የግድግዳ ሰዓት ዘንግ የሙስሊም ሳይንቲስቶች የፈጠራ ውጤቶች ናቸው:: ብዙ ወሳኝና መሠረታዊ አሳቤዎችን ለምሳሌ:- “አልጀብራ” የዐረብኛ ቁጥር (አሁን የምንገለገልበት “እንግሊዝኛ” (ዜሮ) ቁጥር (ለሂሳብ እድገት ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያበረከተ) በመካከለኛው ዘመን ለነበሩ አውሮፓውያን ያስተዋወቁት ሙስሊም ምሁራን ናቸው:: ኢስላማዊ አስተምህሮ የአውሮፓ የሳይንስ አብዮት እንዲያብብና እንዲመነጥቅ ያደረገውን ሳይንሳዊ ንቃተ-ህሊና ፈጥሯል::

በሙስሊሙ ዓለም የሳይንስና የሳይንሳዊ ውጤቶች ዕድገት የተገታው ከዚህም አልፎ ፋናው የጠፋው ሰዎች ከመሠረታዊ የኢስላም መመሪያና እምነት ማፈንገጥ ሲጀምሩ ነው::

## 20. አክራሪነትና አሸባሪነት

Fundamentalism (አክራሪነት) የሚለው የመጣው Fundare ከሚለው ሥርወ-ቃል ነው:: ይህም “መሠረት” ማለት ነው:: አክራሪነት ከኃይማኖት አንፃር ስናየው በኃይማኖቱ አናቅፅ ጥሬ ትርጉም ማመን ነው::

ለምዕራባዊያን "ሙስሊም የሚል ቃል ስትሰሙ መጀመሪያ ፊታችሁ ድቅን የሚለው ምስል ምንድነው?" ብለህ ብትጠይቃቸው አብዛኞቹ "አሸባሪ" ብለው ይመልሱልሃል:: ለዚህም ምክንያት ምናልባት አብዛኛውን ጊዜ በሚዲያ ሙስሊም የሚለው መጠሪያ ከአሸባሪ ጋር ስለሚወሳ ይሆናል::

አንድ አይሁድ ወይም ክርስቲያን ግልፅ የሆነ የአሸባሪነት ተግባር ቢፈፅም አይሁድ አሸባሪ ወይም ክርስቲያን አሸባሪ ተብሎ ሲጠራ አይሰማም:: ጂም ጆንስ (ኢየሱስን እወክላለሁ የሚል አሸባሪ ነው) ክርስትናን የሚወክል ተደርጎ እንደማይወሰደው አሸባሪዎችም ሙስሊሙን የሚወክሉ ተደርጎ ሊወሰዱ አይገባም::

"ሙስሊም አክራሪ" እና "ሙስሊም አሸባሪ" የሚሉት ቃላት ብዙውን ጊዜ እየተተካኩ ሲጠቀሱ የሚሰሙ ናቸው:: "ሙስሊም አሸባሪ" የሚለው ቃል በራሱ እርስ በርሱ የሚቃረን ነው:: ኢስላምን በትክክል የሚተገብር ሰው በፍፁም አሸባሪ ሊሆን አይችልም:: አክራሪ የሚለውን ቃል ትርጉም ብናይ አክራሪና አሸባሪ የሚሉትን ቃላትን እያተካኩ የሚጠቀሙት ሆን ብለው ወይም በስህተት መሆኑን እንረዳለን:: በትክክል ስናየው ግን ሁለቱ ተቃራኒ የሆነ ትርጉም እንዳላቸው ግልፅ ይሆንልናል:: እውነተኛ ኢስላማዊ አክራሪ የሚባለው በቁርዓንና በሐዲስ የተጠቀሱ የኢስላም መሠረታዊ መመሪያዎችንና አስተምህሮዎችን ሙሉ በሙሉ የሚተገብር ነው:: ይህ ደግሞ ሰዎች ብዙውን ጊዜ "ኢስላማዊ አክራሪነት" ብለው ከሚጠሩት የተለየ ነው:: በኢስላማዊ አክራሪነት በአንድ ሰው ሰብዓዊነት ላይ የሚፈፀም ጥቃት አሰቃቂ የበቀልና የጥላቻ ተግባራት ለፖለቲካ ጥቅም

ተብለው የሚፈፀሙ የነፍስ ማጥፋት ተግባራት ወይም የሌላ እምነት ተከታይ ላይ ጫና ማድረግን በፍፁም ሊያይ አይችልም። እነዚህ ተግባራት በሙሉ በኢስላም በግልፅ የተከለከሉ ናቸው። ነቢዩ ሙሀመድ (ሰ.ዐ.ወ) ከፍ ያለ የርኅራኄ፣ የለጋሽነትና የጨዋነት ቁንጮ ነበሩ።

ወደ መገናኛ ስንመጣ የመገናኛ ብዙሃን ፓውዛ በተደጋጋሚ ሙስሊም አክራሪ ተብለው በሚጠሩ ነፍሰ ገዳዮች አሸብርቋል። ያኔ ኢስላም በትክክል ከሚተገብሩት ትክክለኛ "ሙስሊም አክራሪ" ከሚባለው ትርጓሜ ጋር ሙሉ ለሙሉ ይቃረናል። በጣም የሚያሳዝነው ብዙ ሰዎች ስለ ኢስላምና የኢስላም መሠረታዊ የእምነት ክፍል ናቸው ተብለው በስህተት በተነገራቸው ነገሮች ላይ በመነሳት መሠረት የሌለው ጭፍን ፍራቻ ማዳበራቸው ነው። በመስቀል ጦርነት ጊዜም በኢስላም ላይ እጅግ በጣም ጭካኔ የተሞላበትና ርህራሄ የጎደለው ተግባር የፈፀሙ አንዳንድ ሰዎች ነበሩ። ሰዎች ኢስላምን እንዲፈሩና በኢስላም ላይ ጥላቻ እንዲያዳብሩ የቁርዓን አንቀፆች ያለቦታቸው በጋዜጣና በመጽሔት ተጽፈው ወይም በሬድዮ፣ በቴሌቪዥን ሞገድ ተለቀው ለሚያነብና ለሚሰማ ሰው ድርጊቱ እጅግ የሚያበሳጭና የሚያሳዝን ነው።[21]

በኃይማኖታዊ አባቶችም ሆነ በአሸባሪዎች የኃይማኖታዊ አንቀጾችን ትርጉም ማዛባትና ያለ ቦታቸው መጥቀስ ርካሽ ተግባር ነው። ኃይማኖታዊ አንቀጾችን ያለቦታቸው ትርጉማቸውን አዛብቶ

---

[21] በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 10 ቁጥር 34 ላይ ዒሳ (ዐ.ሰ) እንዲህ ማለቱ ተጠቅሷል። "በምድር ላይ ሰላምን ለማምጣት የመጣሁ እንዳይመስላችሁ ሰይፍን እንጂ።" ይህም ብዙ ጊዜ ሊተላለፍ የተፈለገውን ቅዱስና ጠቅላላ መልዕክት ሳያገናዝቡ አንዳንድ አንቀጾችን መዞ በማውጣት ያለ አውዳቸው መጥቀሱ ከሃቁ ምን ያህል ሊያርቀን እንደሚችል በሚገባ ያስገነዝበናል።

መጥቀስ ሌላኛው ሽብርተኝነት ነው:: ሽብርተኝነት በአካል ላይና በሥነ-ልቦና ላይ ወይም በስሜት ላይ ጉዳት ማድረስ ሊሆን ይችላል:: ቢያንስ ሽብርተኝነትን ለማስወገድ የሚጥሩ ሰዎች ሁሉ አንዱ የሌላውን ትክክለኛ የእምነቱ እሳቤዎችን የመረዳት ግዴታ አለባቸው ::

የሚያሳዝነው ወደ አንድ ወገን የአደላው የዘመኑ ሚዲያ ያለማቋረጥ በዚህ በማይታወቅ እና እንግዳ በሆነ እምነት የሰዎች ልብ ውስጥ የፍርሃት ነዳጅ እየሞላ መጥፎ ስሜት እንዲቀሰቀስ ማድረጉ ነው::

በጥቂት ሰዎች ቁጥጥር ሥር ያለው የብዙሀኑ መገናኛ የዓለምን አመለካከት በሚፈልጉት መልክ ለመቅረፅ እና የሰውን አእምሮ ለመቆጣጠር በሰው ልጅ እስከ ዛሬ ከተፈበረኩ መሣሪያዎች ሁሉ በበለጠ የተጠናና የጠራ መሣሪያ ሆኖ ተገኝቷል::

ማግለል ነገሩን እጅግ ወደተባባሰ ነገር ውስጥ የሚከት ጉዳይ ነው:: ሁሉም መንግሥታት የሀገር አንድነትን ለማምጣት ብለው የወታደሮቻቸውን ስሜት ለመቀስቀስ ጠላት እንደሚፈጥሩ የታወቀ ነው:: በቀዝቃዛው ጦርነት ጊዜ “እንደጠላት” የተወሰደው ኮሚኒዝም ነበር:: በአሁኑ ጊዜ ሙስሊሞች በዓለም አቀፍ ደረጃ እራሳቸውን በጠላትነት ተፈርጀው ይገኛሉ::

በዚህ አሳዛኝ አጋጣሚ በዓለም ላይ የሚገኙ ኢስላማዊ መመሪያዎችን በትክክል የሚተገብሩ ሙስሊሞች ለመንግሥታቸው እና በምዕራባዊያን መንግሥታት ብቻ ሳይሆን በለዘብተኞች (ዓለማዊያን) እና ጠባብ አዕምሮ ባላቸው አክራሪዎች

መካከል ሆነው እንደ ሙስሊም ኃይማኖታቸውን መተግበር የማይችሉበት ከባድ ችግር ውስጥ ተዘፍቀዋል:: አድሎአዊ የሆነው የመገናኛ ብዙሀን ፓውዛው የሚረጨው የዜና ጩረር በትክክል ኃይማኖታቸውን አጥብቀው ስለሚከተሉ ሰዎች አይደለም::

በዘመናችን በከባድ ጭቆና ውስጥ የሚኖሩ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች አሉ:: አዋራጅ በሆነ አመፅ እና ኢ-ፍትሃዊነት ቤተሰባቸው ተገድሎባቸው፣ ቤታቸው ፈራርሶባቸው የወደፊት ተስፋቸው ጨልሟል:: እንዲህ ዓይነት ሁኔታዎች በሌላው ዓለም ቸል ተብለው ርህራሄ በጎደለው ግዴለሽነት ከተተዉ ሁሉንም ኃይማኖት እና ባህል የሚያዳርስ ተስፋ አስቆራጭ አመፅ ሊቀሰቅስ ይችላል::

ብዙ ሙስሊሞች አሁን የሚገኙት በዚህ ሁኔታ ነው:: ተስፋ ቆርጠው ፊታቸው ለተደቀነው ዋጋ የሌለው አማራጭ ትዕግስት አጥተው ተስፋ በቆረጠ ስሜት ፍትህን ይጠብቃሉ:: በዚህ ምክንያት ገደብ ያለፉ የአመፅ እርምጃዎችን ሲወስዱ ከዚህም አልፈው ፖለቲካዊ ወይም ወታደራዊ እራስን የመከላከል እርምጃ ለመውሰድ ብለው እራሳቸውን እስከ ማጥፋት ሲደርሱ እናያለን:: እራስን ማጥፋትም ሆነ ሠላማዊ ሰውን መግደል በኢስላም የተከለከሉ ተግባራት ናቸው:: በሙስሊም ዓለም የሚኖሩ በጭቆና አጣብቂኝ ውስጥ ያሉ ሰዎች ለሚወስዷቸው ገደብ ያለፉ ተግባራት አመፅ እና ተስፋ የመቁረጥ ስሜት ከኃይማኖት እና ከኃይማኖት ውጪም ሥራቸው ትክክል መሆኑን ለማስረዳት መረጃ ማቅረባቸው አይቀሬ ነው::

## 21. ማጠቃለያ

ኢስላም አብዛኛውን ጊዜ ያለ አግባብ የተወከለና ብዙ ሰዎችም በትክክል ያልተረዱት እምነት ነው:: ኢስላም የሠላም፣ የፍትህ፣ የፍቅር፣ የይቅር መባባልና የምህረት እምነት ነው:: ኢስላም ማለት ፍላጎትን ሠላም ለሆነው አላህ አሳልፎ መስጠት ማለት ነው:: ኢስላም ከአላህ በቀር ሌላ አምላክ የለም:: ከሱም ሌላ ሊገዙት የሚገባ ጌታ የለም የሚለውን ለመረጠ ሁሉ የህይወት መንገድ ነው:: ይህች ዓለም ጊዜያዊ ነች፤ ይህች ዓለምም የሙከራ ዓለም ነች:: ሁላችንም ሞተን ሁሉም ነገር ወደ እርሱ ወደ ሚመለሰው አላህ እንመለሳለን:: ከትንሳዔ በኋላ ያለው ህይወት ቀጣይ እና ዘለ-ዓለማዊ ነው::

ብርሃን የሆነው አላህ የአደም ልጆችን ወደ ቅን መንገድ ለመምራት ኢስላምን የሚያስተምሩ ነቢያትን ኢብራሂም፣ ሙሳ፣ ዒሳ፣ ሙሀመድን ልኳል:: ሙሀመድንም የመጨረሻ ነቢይ አድርጎ መርጧቸዋል:: በሳቸው ላይ ቁርዓኑን በማውረድም የተለየ ፀጋ አጎናጽፏቸዋል::

ቁርዓን ያልተሰረዘ እና ያልተደለዘ ከአላህ በቀጥታ የወረደ እንጂ መጻፍ እና ማንበብ ከማይችሉት ከነቢዩ ሙሀመድ የመነጨ አይደለም:: የሰው ልጆች ሁሉ ቁርዓን በሚያስተላልፈው እውቀት እና መመሪያ እንዲጠቀሙ አላህ ሳይበረዝ እና ሳይደለዝ እንዲቆይ አደረገው:: ወደፊትም እንደሚጠብቀው ቃል ገባ::

አምስቱ የእስልምና መሠረቶች የሚከተሉት ናቸው:-

1. ከአላህ በቀር ሌላ አምላክ የለም:: ነቢዩ ሙሀመድም የአላህ መልዕክተኛ ናቸው ብሎ በልብ አምኖ በቃል መመስከር::
2. ሥርዓቱንና ወቅቱን ጠብቆ በቀን አምስት ጊዜ ሰላት መስገድ
3. በየዓመቱ ከተቀማጭ ብር 2.5% አማካይ ዘካዕ ማውጣት
4. በረመዳን ወር መፆም
5. የቻለ ሰው በእድሜው አንድ ጊዜ ሐጅ ማድረግ::

ጂሀድን መረዳት የግድ ነው:: ጂሀድ ኢስላማዊ ህግጋትንና መመሪያዎችን የጣሰ ሊሆን አይችልም:: ጂሀድ የአላህን ውዴታ ለማግኘት ተብሎ የሚደረግ ትግል ነው:: አሸባሪነት በኢስላም በግልፅ የተወገዘ ተግባር ነው:: በፍፁም ጂሀድ ተብሎ ሊጠራ አይችልም:: አላህ በኃይማኖት ማስገደድ የለም ብሎ አውጇል:: የሰው ልጅ መብቶችና የፈለገውን የመምረጥ ነፃነቱ የተከበሩ ናቸው:: በኢስላም የሴቶች ሚና ከፍተኛ ነው:: ሴቶችና ወንዶች እኩል በመሆናቸው ተገቢው ክብር ሊሰጣቸው ያስፈልጋል:: አላህ በኛ ላይ ፀጋውን በመሙላት ኢስላምን ፍፁምና ለሰው ልጆች በሙሉ መመሪያ አድርጎ እንደመረጠው በቁርዓኑ ገልጿል:: አላህ የሰው ልጆች በሙሉ በኢስላም ብርሃን ተመርተን ወደርሱ እንድንመለስ ኢስላምን አዘጋጀልን::

## 22. የፀሐፊው ማስታወሻ

እፁብ ድንቅ የሆነው አላህ ከነጠላ ህዋስ እንዳስገኘን እናውቃለን:: ይህ የተገኘሁበትን ነጠላ ሴል ሳይንቲስቶች በህዋ ውስጥ ይገኛሉ ብለው ከነገሩን 120 ቢሊዮን ጋላክሲዎች ጋር ሳስተያየው የመጨረሻ ትንሽነት፣ የመጨረሻ ደቂቅነት ይሰማኛል::

ሸይጣን ሰዎችን በማሳሳት በመካከላቸው አለመግባባት፣ ጥላቻ፣ ቂመኝነትና ጦርነት ሊያሰፍን ምሎ ተገዝቷል:: በመግባባት ላይ የተመሠረተ ሠላምን በማበረታታት ፈጣሪዬን ለማስደሰት እና ሸይጣንን ለመቃረን በሚል ነው ይህንን መጽሐፍ ለመጻፍ የተነሳሳሁት::

ህይወት አጭር ግን ክቡር ነች:: ይቺ ሕይወት ትክክለኛው የተፈጠርንበት ዓላማን (አንድ ፈጣሪን ብቻ ማምለክ) በመዘንጋት አላፊ ጠፊ የሆኑ ቁሶችን በማጋበስ ካባከንናት አሳዛኝ ነው:: ብዙ ሰዎች ክቡር ህይወታቸውን ቁሳዊ ሀብት ብቻ በማከማቸት ሲያባክኗት ይስተዋላል:: ፈጣሪ በኢስላም አማካኝነት ትኩረታችንን ማብቂያ ለሌለውና ዘለዓለማዊ ለሆነው የነገ ሕይወታችን እንድናደርግ ይጋብዘናል:: በፍርዱ ቀን ስለ ዕውቀታችንና ስለ አለንበት ሁኔታ እንጠየቃለን:: ያኔ ለሚቀርቡልን ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ ለመስጠት የምንዘጋጅበት ወቅት አሁን ነው::

ይህ መጽሐፍ ላለፉት ሁለት ዓመታት እስልምናን በተመለከተ የሰጠኋቸው ትምህርቶችን በመመርኮዝ የጻፍኩት ነው:: መጽሐፉ ያለ አላህ እዝነትና እርዳታ እንዲሁም ያለ ወንድሞቼና እህቶቼ ትብብር ለፍሬ አይበቃም ነበር:: የዓለም አንድ አምስተኛ ህዝብ እምነት የሆነውን እስልምናን ለመገንዘብ

ይህንን መጽሐፍ ለማንበብ ጊዜያችሁን የሰዋችሁ አንባቢዎቼንም አመሰግናለሁ:: ስለኢስላም ተጨማሪ መረጃ ከፈለጋችሁ www.islam is.com የሚለውን ድህረ-ገፃችንን መጎብኘት ትችላላችሁ:: በዚህ ቀጣይ ሥራችን ላይ ያላችሁን ጥይቄ፣ አስተያየት ወይም ሒስ ከላይ በተገለፀው ድህረ-ገጽ ብትሰጡኝ በደስታ የማስተናግድ መሆኔን ከወዲሁ ለመግለፅ እወዳለሁ::

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በጠቀስኩት ነገር ማንኛውንም ሰው ያስከፋሁ ወይም ያስቀየምኩኝ ከሆነ ይቅርታ ይደረግልኝ:: ለኢስላም ካለኝ ፅኑ ፍቅር የተነሳ እምነቴን በግልፅና በሙሉ ልብ እገልፃለሁ:: ለግለሰቦች ምርጫና ለአመለካከት ልዩነቶች ከፍ ያለ ክብርና ዋጋ እሰጣለሁ:: መግባባትና ፍትህ የሠላም መንገዶች ናቸው::

በምዕራቡ ዓለም እስልምና በጠባብ አመለካከት ታጥሮ ዓለም በኃይል ለመቀየር የሚጥር ኃይማኖት ተደርጎ ይቀርባል:: ስለዚህ ይህንን መሠረተ-ቢስ አመለካከት ለማስቀየር እምነቴን በግልፅና በማያሻማ ቋንቋ ማቅረብ እንዳለብኝ ይሰማኛል:: አላህ ሁላችንንም ወደ ቀናው መንገድ ይምራን:: ከዚህ ሥራዬ ማንኛ ውንም ዓይነት መልካም ነገር ቢገኝ ከአላህ በጎ አድራጊነት ሲሆን የማይጠቅም ነገር ቢገኝበት ከኔ ጉድለት የመጣ ነው:: የተሞገሰውና የተወደደው አላህ ፍፁም ነው::

"ሁሉን ሰሚው አላህ ከክፋት ሁሉ ጠብቀን፣ ወደ እውነት ምራን::"

ሠላም በናንተ ላይ ይሁን::

ፒት ሴዳ

ይህን መጽሐፍ አንብበው ሲጨርሱ ሌሎችም እንዲያነቡት እንዲጋብዙና የዕውቀት በረከትና ፀጋን እንዲያገኙበት በትህትና እንጠይቃለን:: (የአላህ ፍቃድ ይሁን)

እንዲሁም ይህንን መጽሐፍ በትርጉም፣ በጽሑፍ፣ በህትመት እና አስፈላጊውን ትብብር ለአደረጉልን ሁሉ በዱዓችን ልናስታውሳቸውና በአላህ ስም ልናመሰግን እንወዳለን::

ይህንን ፀጋ ለሰጠን አንድ ፈጣሪያችን አላህ ምስጋና ይግባው::

كتب الجاليات

٧ / ١٩٣

مكتب الدعوة بالسلي

هاتف ٠١١٢٤١٠٦١٥ تحويله ٥٥٥ - ٠١١٢٤١٤٤٨٨ ناسوخ ٢٣٢

السلي

# التعريف بالإسلام




حساب التبرعات بمصرف الراجحي : SA2280000296608010070509

حساب التبرعات بمصرف الإنماء : SA5305000068200517913000

حساب التبرعات بنك البلاد : SA5615000999115390770007

حساب الزكاة بمصرف الراجحي : SA1180000296608010070707

الأمهرية